ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 10፣ ሕዳር 2008

## የጋራ ዕይታ በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)





Students' graduation with second degree in Construction Engineering at BIT

page 5

## ዱላና ዱለኝነት እስከ መቼ?

ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

## Revisiting (Good) Governance: A Topical Issue for further Research?

Chalachew Tarekegne

## ጉድ ሰራችኝ

ሂሩት አድማሱ



Dr Alemayehu kebede, Debre Tabor University's president, congratulating the novice graduates of College of Medical and Health Sciences at BDU





BIT and EiTEX organized the 3rd national Univeristy - Industry Linkage workshop themed as "University Industry Linkage for Better Internship Practices and Technology Transfer"

... page 4

Photo Gallery
page 16

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
አቶ እምቢያለ በየነ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ፈታሒ በቃሉ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ይናገር ተ/ስላሴ
አብነት ሰለሞን
እየሩስ ካሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ቻላቸው ታረቀኝ
ሂሩት አድማሱ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ



ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# ምሁራን ለላቀ ዕድገት ያላቸውን ሚና እንዲያሳድጉ እንደግፋለን!!!

‹‹የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተሳትፎ ለላቀ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን›› በሚል መሪ ቃል በአገር አቀፍ ደረጃ ለአስረኛ ጊዜ የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በአል በድምቀት ተከብሯል፡፡ በበአሉ ላይ የትውልድ ባለአደራ የሆኑት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የመጡበትን ማህበረሰብ የሚወክል አልባሳትን በመልበስ ባህላዊ ጭፈራዎችና ውዝዋዜዎች አቅርበዋል፡፡ በበአሉ ላይ ለዘመናት የዘለቀውን የአንድነት ፅናታችንን ውጤታማነት ለዓለም ህብረተሰብ አጉልቶ ለማሳየት እና አገራዊ ለውጥ በሁለንተናዊ መልኩ ለማረጋገጥ ሁሉም በተሰማራበት የስራ ዘርፍ ጠንክሮ መስራት እንደሚኖርበት ይታመናል፡፡

ለሀገራዊ አንድነት መጠናከር እና ለህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት መረጋገጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከትም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የራሱን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ውጤታማነት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን የላቀ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ምሁራን አገርን ለማልማትም ሆነ ለውጥን ለማምጣት ከተንቀሳቀሱ እንዲሁም በተሻለ ጥረትና በጋራ ተነሳሽነት የሀገራችንን ገፅታ ለመቀየር አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ወጣቱን ኃይል በዕውቀትና በክህሎት በመደገፍ በትውልድ ቅብብሎሽ ሀገራዊ ግንባታውን የማሳለጥ ትውልዳዊ አደራ አለባቸው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችም በሀገሪቱ የተቀጣጠለው የድህነት ትግል እልህ አስጨራሽ መሆኑን በመገንዘብ ተቋማቱ ያስታጠቋቸውን ዕውቀትና ክህሎት ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሀገርን ወደ ከፍታ ማማ የመውሰድ የድርሻቸውን መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት የተቋማቱ የተማረው የሰው ኃይል አገራዊውን የአንድነትና የጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ በእውቀትና በክህሎት በመምራት፣ በማስተባበርና በመደገፍ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን እውቀታቸውንና ኃላፊነታቸውን በምርምርና በጥናት በመደገፍ ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን በመስጠት ሀገርንና ወገንን የሚጠቅሙ ስራዎችን መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የምሁራኑን የምርምር ስራዎች የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የውይይት፣ የምክክርና የግንዛቤ ማዳበሪያ ዝግጅቶችን ተከታታይነት ባለው መልኩ ማቅረብ እንደሚገባ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያምናል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በሀገር ህልውናና ዘላቂ ጥቅም ላይ ወሳኝነት ባላቸው ብሄራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረጉ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየት መምከርና መዘከር እንዲሁም የየኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ድርሻ መሆኑን ተገንዝቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ወደፊትም አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በሀገራዊው እድገትና በዜጎቿ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ የእውቀትና ክህሎት ባለቤት የሆኑት የተቋሙ ምሁራን ድርሻ ጉልህ ሚና እንዳለው ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓልና ሌሎችም በአላትን ስናከብር በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተውን አንድነት በማጠናከርና የባህል ልውውጥ በማድረግ፣ በዘርፉ እውቀትን በማበልጸግ ዘላቂ እድገትንና የጋራ ተጠቃሚነትን ትርጉም ባለው መልኩ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ስለዚህ አገራዊ ለውጥ ለማምጣት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን የጎላ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ዩኒቨርሲቲያችን ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል እናረጋግጣልን!

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የጋራ ዕይታ በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የሰው ልጅ አመለካከቱንም ሆነ ተግባሩን የሚወስኑት በዋናነት ባለው እይታ እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ ራዕይ ጥበብ 2017ን ለማሳካት እየጣርን ያለው ደግሞ የአመለካከትና የተግባር ተደጋጋፊነት በማረጋገጥ በድምር ስራችን ያቀድነውን ለማሳካት ነው፡፡ የአመራሩን፣ የመምህሩን፣ የአስተዳደር ሠራተኛውንና የተማሪውን እይታዎች በመፈተሽና በራዕዩ ላይ ቀጣይነት ያለው ውይይት በማድረግ ቢያንስ ልንደርስበት ያቀድነው አላማ ግልጽ ሆኖ ሊታየን ይገባል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት አንድን ነገር የምናይበት መስኮት፣ የምናየው ርቀት፣ ከርቀት ያለውን በሀሳባችን አቅርበን የምናይበት አግባብና ከርቀት ልንደርስበት ያነጣጠርነው ግብ ላይ ለመድረስ የምንመርጠው መንገድ ላይ ያሉ እይታዎች ግልጽ ባልሆኑበትና የሁላችንም በተለያዩበት አግባብ የዜሮ ድምር ጉዞ እንጂ መፈንጠር ቀርቶ መራመድ ስለሚያዳግት እይታዎቻችን ላይ ውይይት እንዲኖር መነሻ ለማቅረብ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን በራዕይ ጥበብ 2017 ዕይታ መመራት ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ በዚህ ራዕይ ላይ እየተወያየና እያዳበረ ተደጋጋፊ እይታዎች እንዲኖሩ መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሠርተዋል፡፡ ራዕዩን በስነ ሀውልት፣ በስነ ስዕል፣ በስነ-መዝሙርና በተለያዩ ድህረ ገጾች ጭምር በመጠቀም ስለመዳረሻ ግባችን፣ ስለመሄጃ መንገዳችንና በጉዟችን ወቅት ሊገጥሙን ስለሚችሉ ችግሮችና መፍትሄያቸው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በዚህም ስራችን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ራዕዩን ለማሳካት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ እየተረባረበ ይገኛል፡፡ በውጤት ደረጃም ረጅም ርቀት እንደሄድን ራዕዩን በሚገባ ለተረዳ ሁሉ ግልጽ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመሆን ጉዳይ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ተረድተን በጋራ በሰራነው ስራ ሳምንታዊ፣ ወራዊ፣ አመታዊ ወዘተ. የምርምር ጉባኤዎችንና ስብሰባዎችን የምናደርግ ተቋም በመሆናችን በርካታ መመራመርና የምርምር ጽሑፍ የሚያሳትሙ መምህራን ማፍራት ችለናል፡፡ የምናሳትመውም የህትመት ብዛት በእጅጉ አድጓል፡፡ በምርምር ያልተደገፈ ትምህርት ብዙም ርቀት እንደማይወስደን አውቀን ምርምርንና መማር ማስተማርን ለማስተሳሰር ከፍተኛ ጥረት እያደረግን ነው፡፡ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲረጋገጥ ተግባር ተኮር ትምህርት፣ ተከታታይ ምዘና፣ ኮርሶች በዘርፉ ብቁ በሆኑ መምህራን እንዲመሩ፣ የተማሪዎች የኢንዱስትሪ ላይ ስልጠና፣ ተገቢ የምዘና ስርዓት በመተገበር የሚያበረታታ ርቀት ሄደናል፡፡

እነዚህን ከላይ በጥቂቱ የጠቃቀስናቸውን ስኬቶች ያስመዘገብነው በማህበረሰባችን ላይ በፈጠርነው የተደጋጋፊ እይታዎች ግንባታ ልክ ነው፡፡ ስለሆነም በራዕያችን ላይ ተወያይተን እይታችንንም የበለጠ የሚደጋጋፍበትን ሁኔታ ፈጥረን ቢሆን ኖሮ ከዚህም በላይ ስኬት እናስመዘግብ ነበር፡፡ በተለያዩ እርከኖች ላይ ያሉ አመራሮች በፍጥነት የመቀያየርና በተመሳሳይ መልኩ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎችም የመለዋወጥን ሁኔታ ያገናዘበ መድረክ እየፈጠርን የሠራነው ስራ ትንሽ በመሆኑ የራዕዩን ሙሉ እይታዎች ካለመገንዘብ የሚመጡ ችግሮች አሉ፡፡ አንዳንዴም ዩኒቨርሲቲውን ከግል የስራ ስምሪትና ባህሪ አኳያ የማየትና በዛ ልክ የመፈረጅ ዝንባሌዎች ይታያሉ፡፡ ከተቋሙ እጅግ ሰፊነት የተነሣና በተለያዩ እርከኖች ያሉ ኃላፊዎች ስራና ሠራተኛን የማገናኘት ውስንነት የተነሣ በቂ ተግባር እንዲፈፀም የስራ ስምሪት ያልተሰጠው ሰው ሁሉም ቦታ ስራ እንደሌለ ቢገምት አይገርምም፡፡ ችግሩ የሚመነጨው ከሁለት አቅጣጫ ነው፡፡ አንደኛው የበላይ አመራሩ የራዕዩን ዕይታዎችንና ዋና ዋና መለኪያዎችን ካለማስረጽ የሚመነጭ ነው፡፡ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎትና በመማር ማስተማር ያለውን ሁኔታ ከዋና ዋና ግቦች አንፃር ልንገልጽ ይገባል፡፡ ሁለተኛው ምንጭ የቅርብ ኃላፊው በቂ ተግባር አለመስጠቱ ነው፡፡ የሚሰጥ ተግባር ከሌለ ደግሞ ስራ ወዳለበት ክፍል አለማዛወሩ ነው፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ስናነሳ የምናይበት መስኮቶች የምርምር መስኮት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት መስኮት፣ የመማር ማስተማር መስኮትና የአስተዳደር መስኮት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የሚመራመረው፣ ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጠውና የሚያስተምረው ሀይል አላማ ፈፃሚው ሀይል ነው፡፡ የሚመዘነውም በራዕዩ የተቀመጠውን አላማ ከማሳካት አንፃር ይሆናል፡፡ በአላማ ፈፃሚ ስር የሚካተቱት ዋነኛ ሀይሎች መምህራን ናቸው፡፡ መምህራን የተሰጣቸውን ተልዕኮ እንዲያሳኩ የሚያስፈልጋቸውን ግብዓትና ድጋፍ መስጠት ላይ ትኩረቱን ያደረገውና ወሳኝ የሆነው አራተኛው መስኮት የአስተዳደሩ መስኮት ነው፡፡ ከዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ ጀምሮ ማንኛውም ኃላፊ ውጤቱ የሚመዘነው መምህራን ተልዕኳቸውን ያሳኩ ዘንድ በፍጥነትና ትኩረት ሰጥቶ ግብዓትና ድጋፍ ከመስጠት አንፃር ነው፡፡ በውጊያ ላይ ያለ ሠራዊት ውሃ፣ ስንቅና ትጥቅ በወቅቱ ካልቀረበለት እንደሚሸነፍ ሁሉ መምህራንም ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ናቸው፡፡ ልንገነዘብ የሚገባው በውጊያ ላይ ካለ ሰራዊት በላይ አድርገን ነው፣ መስለን ነው፡፡ ትውልድን ከመቅረጽ የበለጠ ውጊያ የት አለና!!

በዚህ መነሻነት በተለያዩ እርከኖች ያሉትን አመራሮች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና ተማሪዎች ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን በአራቱም መስኮቶች እንዴት ያዩታል የሚለውን ሀሳብ በማንሳትና ስለ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሲገለጽ መሠረታቸው ከነዚህ እሳቤዎች የመነጩ ናቸው ወይ? ብሎ በመጠየቅ ልንወያይ ይገባል፡፡ አንድ የዩኒቨርሲቲያችን ባልደረባ ሻይ ቤትም ሆነ ስብሰባ ላይ ስለ ዩኒቨርሲቲው የሚሰጣቸው ሀሳቦች መሠረታቸውን ለመረዳት መሞከር በአጠቃላይ የአመለካከታችንን መሰረት ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ በእውነተኛ መረጃ ተመስርተን የመናገር ባህል ያዳብርልናል፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብም የሚሰራውን ስራና የቀን ተቀን የውሎ ተግባሩን ከዩኒቨርሲቲው ዋነኛ አላማዎች አንፃር ይመነዝራል፡፡

ሁላችንም ዕውነተኛ መረጃ ላይ ተመስርተን ዕውነት ከተናገርን ዕውነት ደግሞ አንድ ብቻ በመሆኗ ተደጋጋፊነት ያለው ዕይታ እንዲኖረን ያደርገናል፡፡ ዕውነት ሁለት መልዕክት ስለሌላት፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲዎች ከኢንዱስትሪው ጋር በመቀናጀት መስራት እንዳለባቸው ተጠቆመ

ከየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስቴይልና ፋሽን ዲዛይን እና የቴክኖሎጂ ተቋማት ከGIZ ጋር በመተባበር 3ኛውን አገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲዎች የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም አካሄዱ፡፡ የፎረሙ ዋና ዓላማ በሁለተኛ ዙር ውይይት በተደረገባቸው ነጥቦች ላይ የተሄደባቸው ሂደቶችና ተግዳሮቶችን በመለየት ለወደፊት ከእነዚህ ችግሮች በመነሳት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ማዕከላት ያለው የቁጥር አለመጣጣምና አለመግባባት በዘላቂነት መፍትሄ መስጠት የሚያስችል የጋራ መግባቢያ ሐሳብ ማስቀመጥ ነው፡፡

ፎረሙን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር በተጨማሪ የምርምር ተቋም ለማድረግ በሳይንስና የሳይንስ ውጤቶች፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በምርምር ተግባር ላይ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በቅርበት ሆኖ ጠቃሚ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በፎረሙ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በሚኒስትር ድኤታ ማዕረግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሲሳይ ገመቹ እንደገለፁት የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከኢንዱስትሪው፣ ከልማት ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች፣ ከክልሎች እና ከመንግስት የምርምር ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር አናሳ በመሆኑ በምርምር ዘርፉ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በተፈለገ መንገድ እየተወጡ ባለመሆኑ ይህንን የተለመደ አሰራር ከስሩ በመለወጥ ከኢንዱስትሪ ማዕከላትና ልማት ድርጅቶች ጋር ጥምረት እየፈጠሩና የጋራ እቅድ እየቀረጹ የኢንዱስትሪን እንዲሁም የሕብረተሰቡን ችግሮች በመለየትና ምርምር በማካሄድ ሳይንሳዊ መፍትሔ መስጠትና መደገፍ በሚያስችል አሰራር መደራጀት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር እና የምርምር ሥራዎቻቸው ከተለመደ አሰራርና አካሄድ በማውጣት ከአጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት በማሕበረሰቡ ላይ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ተግባር ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በፎረሙ ላይ ተጠቁሟል፡፡ በመጨረሻም በመንግስት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪ ማዕከላት ያለው የፍላጐት አለመጣጣም በማጥበብ ተማሪዎች በፅንሰ ሐሳብ ያገኙትን እውቀት ከማምረቻ ማዕከላት ትስስር ተፈጥሮላቸው እውቀታቸው በተግባር የሚፈትኑበት አሰራር ለመዘርጋት የሚመለከታቸው አካላት የራሳቸውን የቤት ሥራ ወስደዋል፡፡

## ማዕከሉ ለሴት ሥራ ፈላጊ ወጣቶች የንግድ ሥራ ፈጠራ ስልጠና ሰጠ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንተርፕርነርሽፕ ልማትና ማበልፀጊያ ማዕከል ያዘጋጀው የንግድ ሥራ ፈጠራ ስልጠና ከሁሉም ክፍለ ከተማ ለተመለመሉ ሴት ሥራ ፈላጊ ወጣቶች በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ግቢ በሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ለሁለት ቀናት ተሰጠ፡፡ ወጣቶቹ በባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ አማካኝነት የተመለመሉ ናቸው፡፡

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ተወካይ ዶ/ር ዋሴ አንተነህ ለተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው ዩኒቨርሲቲው በሶስት አበይት ተግባራት ላይ ማለትም በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ ሰልጣኞች ያገኙትን እድል መጠቀም ይችሉ ዘንድ በውይይቱ ወቅት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ለወደፊት በራሳቸው መተማመን እንዲችሉና የይቻላል መንፈስ አንግበው በተሰማሩበት የሥራ መስክ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ ዶ/ር ዋሴ አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ባስገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ያሉትን የንግድ መስሪያ ቦታዎች ለሌላ ወገን ቢያከራይ ለዩኒቨርሰቲዉ ብዙ ገንዘብ እንደሚያስገኙ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በዩኒቨርሲቲው ተከበረ

በሙሉጎጃም አንዷለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ‹‹የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተሳትፎ ለላቀ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን›› በሚል መሪ ቃል በአገር አቀፍ ደረጃ ለአስረኛ ጊዜ የሚከበረውን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓልን አከበረ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁና የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ የሠው ልጅ ስልጣኔ ለማምጣትና ለእድገት የሚሯሯጥ ቢሆንም የራስን ማንነት አውቆ እና የሌላውን አክብሮ በመቻቻል መኖር የላቀ ጥበብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ዶ/ር ባይሌ አያይዘውም ዓለም ወደ አንድ መንገድ እየመጣች ስለሆነና ከዚህም በዋናነት ተጠቃሚው ተማሪዎች ስለሆኑ የራስን ማንነት አውቆ ሌሎችን ሳይጋፋ እንዲሁም ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ራሱን በማጣጣም በኃላፊነት ለመኖር መጣር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡

የበዓሉ የክብር እንግዳ የአማራ ክልል የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር አቶ ንጉስ ጥላሁን በበኩላቸው በዓሉ ህገ መንግስቱ ያጎናጸፈንን ዲሞክራሲያዊ አንድነት የምናንፀባርቅበት በዓል በመሆኑና ዩኒቨርሲቲውም ከአራቱም አቅጣጫዎች የተውጣጡ ብሔር ብሔረሰቦች ስብስብ በመሆኑ መቻቻልንና መከባበርን በላቀ ሁኔታ የምናስቀጥልበት ነው ብለዋል፡፡ ተማሪዎች ከቀለም ትምህርት ባሻገር በመቻቻል ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ እሴቶችን ማዳበር እንደሚገባቸው አቶ ንጉስ አስገንዝበዋል፡፡

በዝግጅቱ ወቅት የባሕል ማዕከል ተማሪዎች የዘጠኝ ክልሎችን የሚወክሉ አልባሳትን በመልበስ የሠልፍ ትርዒት፣ የሙዚቃ ዝግጅት፣ መልዕክት አዘል ግጥሞችና መነባንብ የቀረቡ ሲሆን በክብር እንግዳውና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አማካኝነት የዳቦ ቆረሳ ስነ-ስርዓት ተካሂዷል፡፡

## ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን በዩኒቨርሲቲው ተከበረ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ስነ ባህርይ ፋኩልቲ፣ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት እና የተማሪዎች ህብረት በመተባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ24ኛ ጊዜ፣ በሀገራችን ለ23ኛ ጊዜ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ለ3ኛ ጊዜ የአካል ጉዳተኞች ቀንን “አካል ጉዳተኞችን ማካተት ወሳኝ ነው፤ ተደራሽነትና ማብቃት ለሁሉም” በሚል መሪ ቃል ተከበረ፡፡

በእለቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የትምህርትና ስነ ባህርይ ፋኩልቲ ም/ዲን አቶ እንግዳየሁ ተገኘ ፋኩልቲው በልዩ ፍላጐት እና አካቶ ትምህርት ዘርፍ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ መሆኑን ገልፀው ለ3ኛ ጊዜ በዓሉን የአካል ጉዳተኞችን መብት በማክበር እና በማስከበር እንዲሁም አካል ጉዳተኞች የህብረተሰቡ አካል በመሆናቸው መስራት እንደሚችሉ የሚያመላክትና ማህበረሰቡ ያለውን አመለካከት ክፍተት ለመቅረፍ እንደሚያስችል ተናግረዋል፡

የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር አልማዝ ... በበኩላቸው አካል ጉዳተኞች ባሉባቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጫና ምክንያት በሁሉም ዘርፎች እኩል ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ገልጸው አካል ጉዳተኞችን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው በሁሉም ዘርፍ ተሳታፊ ለማድረግ እንዲሁም ብቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች መመቻቸት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ ዳይሬክቶሬቱ ከ2007 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ የሠራውን ሥራ ዶ/ር አልማዝ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

በእለቱ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሥነ-ጽሑፍ፣ መዝሙር እና የሩጫ ውድድር ያደረጉ ሲሆን ሙሁራን ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተያያዘ ጥናታዊ ጽሑፎችን አቅርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

## መጽሐፍ ተመረቀ

በየማነ ገብሩ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕል ጥናት መምህር በሆኑት በአቶ ሰሎሞን ተሾመ ‹‹ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ›› በሚል ርዕሰ የተጻፈ መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋ ማበጸልጊያ ተቋም አማካኝነት በዩኒቨርሲቲው ሴኔት አዳራሽ ተመረቀ፡፡ መጽሀፉ በስምንት ምዕራፍ ተከፍሎ 336 ገጽ ይዘት ያለው ለመማር ማስተማር ማጠቃሻ የሚያገለግል የተፃፈ ነው፡፡

በምርቃ ስነ-ስርዓቱ በክብር እንግድነት የተገኙ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ እንደተናገሩት መጽሐፉ በዩኒቨርሲቲው ባልደረባ የሆኑት አቶ ሰሎሞን የምርምር ውጤታቸውን ለመማር ማስተማር በሚመጥንና በሚመች መልክ በማሰናዳት ለህትመት ማብቃት በራዕይ 2017 ስኬት ላይ ተቋሙ ምን ያክል ወደፊት እየተራመደ መሆኑን አንድ ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም መጽሐፉ ሲመረቅ በትምህርት ክፍሉ ብሎም በተቋሙ ውስጥ ላሉ ምሁራን ትልቅ መነቃቀት ይፈጥራል ብለዋል፡፡ እንደዚህ የሚታይ ሥራ መሥራት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እና መምህራን ስራዎቻቸውን እውን ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው ያልተወሰነ ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል፡፡

የፎክሎር ምሁራን የሆኑት ዶ/ር ጥላሁን ተሊላ እና ዶ/ር ዋልተንጉስ መኮንን በሥነ-ስርዓቱ ላይ ተገኝተው ሙያዊ ግብረ መልስ የሰጡ ሲሆን መጽሐፉም የባሕል ብዝኃነት ላላት ሀገር የፎክሎር ጽንሰ ሐሳብ ወደ ማህበረሰቡ በቀላሉ ለማስረጽ በሚረዳ መልኩ የተዘጋጀ መጽሐፍ መሆኑን ገምግመዋል፡፡

# አበይት ዜናዎች...

## ተመራቂዎች ያገኙትን እውቀትና ክህሎት በተግባር ላይ በማዋል ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ተገለጸ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለስድስት ዓመታት ያሠለጠናቸውን 93 ወንድና 9 ሴት በድምሩ 102 የህክምና ዶክተሮችን በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ አስመረቀ፡፡ በውጤታቸው ብልጫ ላስመዘገቡ እጩ ተመራቂዎች የሜዳሊያ ሽልማት ተሠጥቷል፡፡

በምረቃው ስነ-ሥርዓት ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለተመራቂዎችና ለቤተሰቦቻቸው የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ ተመራቂዎች ላለፉት ስድስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ የትምህርት ጉዞ አልፈው ለዚህ የምረቃ በዓል መድረሳቸው ሀገሪቱ በዘርፉ የምትፈልገውን የተማረ የሠው ኃይል እንደሚያሟል ገልጸዋል፡፡ ተመራቂዎች ወደ ሥራው ዓለም ሲቀላቀሉ ያገኙትን እውቀት በአግባቡ በመጠቀምና ማህበረሰቡን በዘር፣ በፆታ፣ በእምነት እና በፖለቲካዊ አቋም ሳይለያዩ አቅማቸው በፈቀደ መጠን በማገልገል ግንባር ቀደም መሆን እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አለማየሁ ከበደ ዩኒቨርሲቲው ለሶስተኛ ጊዜ የህክምና ዶክተሮችን ለማስመረቅ በመብቃቱ አጠቃላይ የዩኒርሲቲው አመራር አካላት፣ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ታላቅ ደስታ ሊሠማቸው እንደሚገባ ገልጸው ተመራቂዎች ከረጅም ጊዜ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የቴክኖሎጂ ተቋም በኮንስትራክሽን ምህንድስና ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ

በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና ከክልሉ ዲዛይንና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር በሁለተኛ ዲግሪ በኮንስትራክሽን ምህንድስና ያሰለጠናቸውን ሰማንያ ተማሪዎች አስመረቀ፡፡

በምረቃ ሥነ ስርዓቱ በክብር እንግድነት የተገኙት የአማራ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ያየህ አዲስ እንደገለፁት በሀገራችንም ሆነ በክልላችን በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ ያለው የሰው ኃይል እጥረት አነስተኛ በመሆኑ የሕዝቡን ፍላጐት በመመለስ ዙሪያ ያለው ድርሻ ውስን ነው፡፡ መንግስትና የዘርፉ የልማት ድርጅት አካላት ይህንን ችግር ለመቅረፍ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ወደ ሥራ ማሰማራት አማራጭ የሌለው ተግባር መሆኑን ተረድተው ይህንን መርኃ ግብር ማዘጋጀታቸውን ተናግረዋል፡፡ ተመራቂዎችም የተሰጣቸውን እድልና ኃላፊነት በቅንነትና በቁርጠኝነት ሕዝቡን ማገልገል እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ አቶ ያየህ አክለውም ዘርፉ ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ በመሆኑ ምሩቃን ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር በመላበስ የግንባታዎችን

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ዩኒቨርሲቲው ከባሕር ዳር ከተማ ማህበረሰብ ጋር ውይይት አካሄደ

በአምሳሉ ጥላሁን

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲው እና በባሕር ዳር ከተማ ማህበረሰብ መካከል ስላለው ግንኙነት እና ማህበረሰቡ ስለ ዩኒቨርሲቲው ያለው እይታና ግንዛቤ እንዲሁም አስተዋፅኦ ላይ ያተኮረ የግማሽ ቀን ምክክር ተካሄደ፡፡

የዩኒቨርሲቲው የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር፣ በምርምር እንዲሁም በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ማህበረሰቡን ማዕከል ያደረጉ በርካታ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸው ዩኒቨርሲቲው በከተማዋ በአራቱም አቅጣጫዎች ግቢዎችን በመገንባት የከተማዋን እድገት በማፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የውጭ ግንኙነትና ፓርትነርሺፕ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሞገስ አብርሃ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከየት ወደ የት? በሜል ርዕስ የውይይት መነሻ ፅሁፍ ያቀረቡ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ወደ ፊት በከተማው ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ያቀዳቸውን እቅዶች ለመሳካት የከተማው ማህበረሰብ ሚና ጉልህ መሆኑን ገልፀው ባሕር ዳር ከተማ የትምህርት፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ስራ የሚሰራባት ሞዴል ከተማ ለማድረግ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ተሳታፊዎችም በቀረበው ፅሁፍ ላይ በመነሳት ለዩኒቨርሲቲውን ግብአት የሚሆኑ አስተያየቶችን የሰጡ ሲሆን በተለይ በጣና ሀይቅ ላይ ስለ ተከሰተው የእንቦጭ አረም፣ የባሕር ዳር ከተማ ተፋፈስ፣ ስራ ፈጠራ፣ አጫጭር ስልጠናዎች፣ በሴቶች አቅም ግንባታ እና የስፖርትና መዝናኛ ስፍራዎችን ማስፋፋት ዙሪያ ዩኒቨርሲቲው እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል እንዲሁም ከእነርሱ የሚጠበቀውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በውይይቱ መዝጊያ ላይ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት የዩኒቨርሲቲው የቅርብ ተጠቃሚ የሆኑትን የባሕር ዳር ከተማ ማህበረሰብን ወቅታዊና ጠቃሚ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ማወያየቱ እንዳስደሰታቸው ገልፀው ለወደፊት ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰቡን ጥቅም ማዕከል ያደረጉ ስራዎችን አጠናክሮ መስራት እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

## ተቋሙ የአውሮፓ ኮሚሽን ‹ሆርዞን 2020›ን የምርምርና ፈጠራ ፈንድ አሸነፈ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳደር ተቋም ከተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ‘Its4land’ የተባለ የምርምር ሃሳብ ከአውሮፓ ኮሚሽን ‹ሆራይዘን 2020› /Horizon 2020/ ለተባለው የምርምርና ፈጠራ (Research and Innovation) የሶስት ሚሊዮን ዩሮ የምርምር ገንዘብ በጋራ አገኘ፡፡

ተቋሙ ከአፍሪካ ከኬኒያ እና ከሩዋንዳ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከአውሮፖ ከኔዘርላንድ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ተዌንቲ /University of Twente/ እና ከቤልጅዬሙ ሌያቨን

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የቅንጨ አረምን የማጥፋት ዘመቻ ተካሄደ

በአበባ ሀብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ የማህበረሰብ አገልግሎት አካል የሆነውን አካባቢያችን ከመጤ እፅዋት የማጽዳት ዘመቻ ከአብክመ ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር ከሰማዕታት ጀምሮ እስከ ግዮን ት/ቤት አካሂዷል፡፡ በዘመቻው ላይ ተማሪዎችና መምህራን ተሳትፈዋል፡፡

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ የአዝርዕትና ጥበቃ ክሊኒክ የአረም ጥናትና መከላከያ ባለሙያ አቶ አጠቃ አይቸው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በራሱ ተነሳሽነት ቅንጨ ላይ የመከላከል ሥራ ለመስራት ያሳየውን ተነሳሽነት አድንቀው አረሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ አደገኛ ከሚባሉት አረሞች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቀዋል፡፡ ክልሉ በከፍተኛ ሁኔታ የግንዛቤ ሥራ እየሰራ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ አጠቃ ዩኒቨርሲቲውም ከእኛ ጋር እንደሚሆን ባለሙሉ ተስፋ ነኝ ብለዋል፡፡

የቅንጨ አረም በ1970 ዓ.ም በድሬደዋ አየር ማረፍያ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ሲታመን በአማራ ክልልም በስፋት ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡ አረሙ በቀን 25000 እስከ 30000 በዘር እራሱን በማብዛት የእርሻ ቦታን ከግማሽ መሬት በላይ በመቆጣጠር ሌሎች ነባር ዝርያዎችን የማጥፋት አቅም አለው፡፡ በሰው ጤና ላይም ችግር እንደሚፈጥር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

## ዓለም አቀፍ የአፈር ቀን ተከበረ

በየማነ ገብሩ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሥነ አፈር ተመራማሪዎች ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው አካላት ጋር በመሆን ዓለም አቀፍ የአፈር ቀንን አከበሩ፡፡ በእለቱ ለም አፈር በአጠቃቀም ጉደለት ምክንያት በእያንዳንዱ የሕብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ መሆኑን ተገልጿል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የማሕበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተርና በግብርና ሳይንስ ኮሌጅ የሥነ አፈር ተመራማሪና ምሁር ዶ/ር ጌታቸው ፍስሐ ቀደምት የስልጣኔ ማማ ላይ ተቆናጥጠው የነበሩት አያሌ ሀገራት ስልጣኔያቸው ወደ ኋላ እንዲመለስና እንዲቀዛቀዝ ካደረገባቸው ምክንያቶች አንዱ በተለያየ ምክንያት የለም አፈር መቀነስ መሆኑን ገልጸው በሀገራችን የሕዝብ ቁጥር በመጨመር የወል መሬትን ለእርሻ በመጠቀምና በመሬት መጎሳቆል ምክንያት የለም አፈር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በአርሶ አደሩም ብሎም በከተማ ነዋሪው የኑሮ ሁኔታ ላይ ጫና እየፈጠረ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያስቀመጠውን ዓለም አቀፈ የአፈር ቀንን ምክንያት በማድረግ በመሬት አጠቃቀም የታየዉን ለዉጥና ያለዉን እንድምታ አስመልክተው በዘርፉ ምርምር ባደረጉት በዶ/ር እንየው አድጎ እና በዶ/ር ጌታቸው ፍስሐ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡ በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍም አፈር ለሁሉም ነገር መሠረት በመሆኑ አጠቃቀማችንን ማስተካከል ካልቻልን በውስጡ ያሉ ንጥረ ነገሮች ከመቀነስ በተጨማሪ ከአየር ንብረት መዛባት ጋር ሲደመር ምርትና ምርታማነት እንደሚቀንስ ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም የአፈር ክለት መጠበቂያ ዘዴዎችንን መጠቀምና በሁሉም ባለድርሻ አካላት ስለ መሬት አጠቃቀም ግንዛቤ መፈጠር እንዳለበት ተጠቁሟል፡፡

የበዓሉ መከበር ዋና አላማ የአፈር ለምነት መቀነስ ምክንያት የሆኑትን ነጥቦችን መለየትና ያጠቃቀም ሥርዓቱን ምን መሆን እንዳለበት በማህበረሰብ ላይ ግንዛቤ መፍጠርና የተፈጠረውን ግንዛቤ ማስፋት ነው፡፡ በበዓሉ ላይ ከተለያዩ ወረዳዎች የተውጣጡ አርሶ አደሮች፣ የግብርና ተመራማሪዎች፣ በአፈርና አፈር ነክ ምርምር የሚያደርጉት ምሁራን የክልሉ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን በአፈር መቦርቦር ምክንያት የተጐዱ ቦታዎችና በመልሶ ማገገም ላይ የተሰሩ ሥራዎችን ጐብኝተዋል፡፡

## My Reflection

# Revisiting (Good) Governance: A Topical Issue for further Research?

**Chalachew Tarekegne (PhD Candidate)**
**Department of Civics and Ethical Studies**

Good Governance or simply Governance is the reverberation of the current public-policy and political-economy scenario of countries. In the terminology of public administration, good governance is a contemporary player within the context of globalization. In this playing ground, there are three ways of understanding this new development: firstly, it is an attempt to widen the scope of public administration by going beyond formal government; secondly, it is an externally dictated term invented to prescribe aid-conditionality especially for third world countries like Ethiopia; and thirdly, it is genuinely, 3D-intensifying concept to make public administration more open, transparent and accountable to the general public. The 3Ds being Democratization, De-bureaucratization and Decentralization. In this regard, based on a synthesis of literature sources and personal reflections, the aim of this article is to introduce to the research community of BDU so that governance should not be narrowly conceived in the manner the World Bank and other funding agencies have sought to present it to us because, governance needs, by its very nature, a more creative approach to solve problems and dilemmas that lead to searching new opportunities. In other words, it needs to have a fresh look at, particularly, the state-society relationships in today's complex world of governance which is surrounded by complex problems.

In relation to context, there are lots of researchers who explain the shift of balance between government and society away from the public sector and more towards the private sector. This shift, it is indicated, partly, leads to privatization and sometimes to deregulation. Nonetheless, there are also efforts to shift the balance towards a sharing of tasks and responsibilities, towards doing things together instead of doing them alone either by the 'state' or by the 'market'. Such kinds of new patterns of interaction between governments and society have been observed in areas such as community policing programs, environmental protection, participatory planning, monitoring and evaluation, education and other social welfare services. Hence, these new patterns are seemingly aimed at discovering and inventing other ways of coping with new problems or of creating new alternatives for governing overall institutional or societal problems that emerge during the life journey of generations.This search for analternative paradigm brings out the meaning of what we call Good Governance or simply Governance.

The first meaning in terms of widening the scope of public administration, therefore, has been very well explained by researchers who write about it in the context of contemporary global politics and explicates the term governance in the following way: "Governance is a wider phenomenon than government which embraces governmental institutions, but it also incorporates informal, non-governmental, and community-based organizations whereby those persons and organizations within its range of operation move ahead, satisfy their needs, and fulfill their wants". Governance is, thus, a system of rules that is as dependent on intersubjective meanings as on formally sanctioned constitutions, charters, proclamations, and acts. Consequently, it is possible to think of governance without government. That is, it has its own regulatory mechanisms in a range of activities which function effectively although they are not endowed with formal authority. As a result, governance opens up the promises of alternative public administration models which authorize society's alternative collective problem-solving opportunities and strategies. Governance, so comprehended in this way, is essentially, a Network of Multiple Agencies (NMA) and systems of government than a fixed department, institute, directorate or agency.

Hence, governance, in this context, can stand for establishing, operating and creating networks with social institutions. Objectively, it can manifest itself in all formal, non-formal, and informal rules, regulations, decision making procedures, and strategic actions that serve to define social practices and problem-solving activities. For instance, in real life and in our context, there are many forms of civil society organizations (*Edirs, Ekubs, Debos, Mahibers, Senbeties*) and collective self-help groups which organize themselves to achieve common purposes, such as managing funeral ceremony, provision of financial support during shocks and stresses, resolution of local disputes, community defense, water distribution and irrigation, soil conservation activities, forest management, crop harvesting, among others. This implies that governance is a way of crafting social or public institutions as a matter of public concern not private concern. In this platform, the crux of the matter, is that, to get things done through formally constituted governments, agencies, departments, or directorates is not, therefore, the only way available for collective problem-solving strategy. In this conceptualization of governance, there is a need to infer that; for instance, Bahir Dar University may not solve the problems it encounters by only those formally institutionalized departments, faculties, institutes, or research centers. Instead, this understanding of governance informed us to think of establishing Multiple Networks with all formal, non-formal, and informal organizations, groups or individuals.

> ***"good governance is central to creating and sustaining an environment which fosters strong and equitable development, and it is an essential complement to sound economic policies".***

The second meaning of governance is closely associated with International Aid Conditionality. Referring to the contextual circumstances of the Good Governance concept, there are writers who point out that the current Western Aid and Overseas Development Policy have the following three important features. Firstly, the aim of aid has been to promote open, market-friendly and competitive economy. And, it is asserted by them boldly that this policy was included in the new conditionality of structural adjustment lending which was developed in the 1980s after *Thatcherism and Reaganism*. And, later, in the 1990s, it is indicated that two further features have been added to structural adjustment, i.e. priority to democratization and improvement of human rights records, and determination on what has come to be called good governance. Development assistance to developing countries like that of ours Ethiopia has, thus, been subjected to the new rubric of Good Governance as an authorized principle. And, it was in 1989, for the first time, the concept of Governance was emphasized in a World Bank document on Sub-Saharan Africa countries (example, Ethiopia). By good governance was meant, at that time, sound development management which included four key dimensions – public sector management, accountability, legal framework for development; and information and transparency. The Bank document on Sub-Saharan Africa had this to say: "Improving governance would begin with an assessment of the institutional environment (with emphasis on the key governance elements of accountability, rule of law, openness and transparency) which determines the patrimonial profile of the country: high when all other factors are absent and low when they are present". As the Bank's document, entitled Governance and Development (1992), puts it, "governance is defined as the manner in which power is exercised in the management of a country's economic and social resources for development".

From its long experience in many developing countries like Ethiopia, the Bank came to realize that "good governance is central to creating and sustaining an environment which fosters strong and equitable development, and it is an essential complement to sound economic policies".

Still, a more pronounced political meaning of Governance appeared in the policy directives of the OECD countries, laying down conditionality for receiving economic assistance. The OECD documents sought to link development assistance with participatory development, human rights, and democratization. Moreover, three key components of Governance were also identified namely legitimacy of government, accountability of political and official elements of government, respect for Human Rights and the Rule of Law ( including individual and group rights and security, a legal framework for economic and social activity, and participation). Hence, what is materialized out of the joint efforts of the aid-giving countries and the international funding agencies is that entitlement to aid would depend on

continued on page 13

# ዱላና ዱለኝነት እስከ መቼ?

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

## “የወንድ ልጅ ስራ”

ዘጋቢ ፊልም ለመስራት ዝግጅት ላይ በመሆናችን መረጃ እየሰበሰብን ነው - በድምፅም፣ በምስልም፡፡ እናም ሰሜን ወሎ ውስጥ የቆቦ ጊራና መስኖ ልማት ተጠቃሚ በመሆኑ ኑሮው ትርጉም ባለው መንገድ የተለወጠ አርሶ አደርን የራስ ፀጉር ማስተካከል አስፈላጊ ሆነ፡፡ አርሶ አደሩ ፈቃደኛ በመሆኑ በቢሯችን መኪና አሳፍረን “ሮቢት” ወደምትባለው የገጠር ትንሽ ከተማ አመራን፡፡

ፀጉር አስተካካዩ - “በውላችን” መሰረት - የአርሶ አደሩን ፀጉር ሙልጭ አድርጎ አነሳው፡፡ አስተካክሎ እንደ ጨረሰ ግልፅ የሆነው ነገር በመጠኑም ቢሆን አጎፍሮ ከነበረው ፀጉር መወገድ ይልቅ የአርሶ አደሩ የራስ ቅል በብዙ ሰንበሮችና ለምጦች የተወረረ መሆኑ ነበር፡፡ ነገሩ በጣም ስላስገረመን ያ ሁሉ ሰምበርና ለምጥ ከአናቱ ላይ እንዴት ሊኖር እንደቻለ ጠየቅነው፡፡

“ቆቦ ውስጥ አናቱ ላይ ሰምበር የሌለው ሰው አታገኙም” አለን፡፡

እንደ አርሶ አደሩ አባባል ከሆነ ወንድ ልጅ የሚለካው በወንድ ልጅ ስራ ነው፡፡ ከወንድ ልጅ ስራ አንዱ ደግሞ መፋለም፣ በዱላ መጋጠም ነው፡፡ ሳይመታና ሳይይመታ [“ያለቦታው” ፊደል ከደገምኩ፣ የተደገመውን ፊደል ቀድሞት ከተፃፈው ፊደል ጋር ጠበቅ አድርጋችሁ አንብቡልኝ] ያደገ ወንድ ከሴት ነው የሚቆጠረው፡፡ እሱ ጀግና ሳይሆን ቦቅቧቃ (ፈሪ) ነው፡፡ ሲመቱና ሲመመቱ ደግሞ መፈንከትና መፈንንከት ያለ ነው፤ እናም ሰምበርና ለምጥ ከአናት ላይ ይወለዳሉ፡፡

ዘጋቢ ፊልሙ ከቆቦ ከተማ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ቢያስተዋውቀኝም ከዚያ ወዲህ በተለያየ አጋጣሚ መለስለስ ብዬ አይቻታለሁ - አየሯም ብቻ ሳይሆን እንቅስቃሴዋም ያቅሟን ያህል ሞቅ ያለ ነው፣ በተለይ ከተሲአት በኋላ፡፡ ጥቂት የማይባሉ ሳይክለኞች የእንቅስቃሴዋ አካል ናቸው፡፡ አብዛኞዎቹ ሳይክለኞች ዱላ ይዘው ነው የሚከንፉት፡፡ የሳይክል ነጂዎች እዚህ ላይ መገረማቸው አይቀርም - ዱላ ይዞ ሳይክል መንዳት በጣም አስቸጋሪ ነውና፡፡ ቆቦዎች የሚያደርጉት እንዲህ ነው፤ የዱላቸውን አንድ ጫፍ ከሳይክሉ የቀኝ መሪ ጋር ደርበው ይይዙና ሌላውን ጫፍ ደግሞ ከቀኝ ትካሻቸው ላይ ያሳርፋታል፡፡ ይህም ቢሆን አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ዱላው እስከ ተፈለገ ድረስ ምን ይደረግ?

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ “ዱላው ለምን ተፈለገ?” የሚለው ነው፡፡ አርሶ አደሩ እንዳለው “ወንድ ልጅ ሳይመታና ሳይይመታ” ማደግ ስለሌለበት? ወይስ መንገድ ላይ ጠላት ሊያጋጥም ስለሚችል? ወይስ ባጋጣሚም ቢሆን አምቧጓሮ ሊነሳ ስለሚችል? ወይስ…?

ሳይክለኛውን ሁሉ ሊደባደበው ወይም ሊፋለመው የተዘጋጀ ጠላት አለው ለማለት ያስቸግራል - ሰው ሁሉ ጠላት በጠላት ሆኖና ለመደባደብ ተዘጋጅቶ አይኖርምና፡፡ “ባጋጣሚም ቢሆን አምቧጓሮ ወይም ጠብ ቢነሳ” ብሎ ዱላ መያዝ በመጠኑም ቢሆን ሚዛን ሊያደፋ ይችላል - ከልክ በላይ የሆነን ተጠራጣሪነት ማመላከቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፡፡ ጠብና አምባጓሮ ሳይጠበስ የሚሸታቸው ሰዎች ከዚህ በከፋ ሁኔታ ተጠራጣሪ መሆናቸውን ለመረዳት የፈለገ የፋከራ ግጥማቸውን ማንበብ በቂው ሊሆን ይችላል፤

“ተራራውን ወጥተን

ቁልቁለቱን ወርደን

ወንዙን ስንሻገር

አለ ነገር፣ አለ ነገር…”

## ዱላ መያዝ ለምን?

እዚህ ላይ ዱላ (ወይም እንደ የአካባቢው አጠራር በትር ወይም ሽመል) እሚባል ነገር በፍፁም አያስፈልግም የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ እያነሳሁ አይደለም፤ በአንዳንድ ሁኔታ ሊያስፈልግ ይችላል፣ ለምሳሌ በጨለማ ለሚጓዝ ሰው፡፡ አንደኛ - ዱላ በመያዙ ምክንያት በሌባ ወይም በዘራፊ የመደፈር እድሉ ጠባብ ነው፤ ሌባው ወይም ዘራፊው በቡድን ያልተደራጀ ወይም የጦር መሳሪያ ያልያዘ እስከሆነ ድረስ፡፡ ሁለተኛ - ተጓዡ ጨለማውን ሰንጥቆ ለመሄድ የልብ-ልብ ያገኛል፤ አብዛኛው ህብረተሰባችን ዱላ በመያዝ ባህል ውስጥ ስላለፈ፣ ዱላ መያዝ በልብ ውስጥ የሚፈጥረው በራስ መተማመን አለ፡፡

በድብደባና በነፍስ ግድያ ወንጀል ውስጥ ደግሞ ዱላ ትልቁን ሚና መጫወቱ አንድና ሁለት የለውም፤ “ለምን?” ቢሉ አብዛኛው አርሶ አደር የጦር መሳሪያ የለውምና፡፡

እዚህ ላይ አንድ የራሴ የወጣትነት ዘመን ገጠመኜ ትዝ አለኝ፡፡ ወቅቱ ረመዷን (የፆም ወር) በመሆኑ ወደ መስጊድ ለመሄድ በምሽት ከቤት ወጣሁ፡፡ ጨለማው ከየትም ተጠራርቶ የኛን ሰፈር የወረረው ይመስል አይን በወስፌ ቢወጋ አይታይም፡፡ ዱላዬን በአንድ እጄ እንደ ያዝኩ በሁለተኛው እጄ ባትሪዬን እያበራሁ ከቤታችን ወደ ዋናው ጎዳና የምታደርሰውን ቀጭን መንገድ ጨርሼ ከዋናው ጎዳና ስደርስና ኩኩኩ…ው፣ ዱዱዱ..ው የሚል ከፍተኛ ድምፅ ሲፈጠር አንድ ሆነ፡፡ እናም የእጅ ባትሪዬን ብርሀን አግድም ለቀኩት፡፡ አንድ ረጅም፣ ትልቅ ሰውዬ ዱላውን በኮረትና በጠጠር በተሞላው መንገድ ላይ እየጎተተ፣ ኮረቱን በጫማው ጭምር እየነዳ በጨለማው ውስጥ በመሮጥ ላይ ነው፡፡ የባትሪውን ብርሀን ይበልጥ ረዘም አድርጌ ለቀኩት፡፡ ነጣ ያለች ጥንቸል፣ ከሰውዬው ትንሽ ፈንጠር ብላ የነፍስ አውጭኟን በመሮጥ ላይ ናት፡፡ ረጅም ዱላ የያዘው፣ ረጅሙ ሰውዬ ያን ሁሉ ኳኳታና ዷዷታ የፈጠረው ከፊቱ ያለችው ምስኪን ጥንቸል ገና መሸት ሲል ጀምሮ ሰፈራችንን ከሚቃኟት ጅቦች አንዱ መስላው ነው፡፡ “ትልቅ ዱላ ባይመቱበት፣ ያስፈራሩበት” ማለት ይሄ ነው፡፡

እጅግ ብዙዎቹ በገጠር የሚኖሩ ወንዶች በትር ወይም ዱላ ሳይዙ አይንቀሳቀሱም፡፡ ህፃናቱ ከብቶቻቸውን ይነዱበታል፤ ይመልሱበታል፡፡ ወጣቶቹና ትልልቆቹ ከዚህም በላይ ላለፈ ተግባር ያውሉታል፡፡ እራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ይጠቀሙበታል፤ መንገድ ላይ አውሬ ወይም ጠላት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ - በተለይ ወደ ገበያ ሲሄዱ - እቃ ሊያንጠለጥሉበት ወይም በትከሻቸው የተሸከሙትን እህል የያዘ አቅማዳ ወይም ጆንያ ሊደግፉበት ይችላሉ፡፡ ምንም ይሁን ምን ወደ የትም ቦታ ሲሄዱ ባብዛኛው ዱላ አይለያቸውም፡፡ አንድን የገጠር ሰው ለምን በትር ወይም ዱላ እንደሚያዝ ብንጠይቀው የሚሰጠን መልስ “ወንድ ልጅ ባዶ እጁን አይሄድም” የሚል ድፍን ያለ መልስ ሊሆን ይችላል፡፡

እዚህ ላይ ዱላ ለመያዝ የሚቀርቡ፣ ማለትም ወንድ ልጅን ከዱላ ጋር የሚያቆራኙ ምክንያቶችን ትንሽ ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በአንድ በኩል በርካታው ደን ተመንጥሮ ስላለቀ፣ ለመደበቂያ የሚሆን ጫካ ብዙም ስለሌ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንዱን የገጠር ቀበሌ ከሌላው የሚያገናኝ መንገድ በመስፋፋቱ አውሬ ለመንገደኛ ስጋት የመሆን እድሉ እጅግ በጣም ጠባብ ነው - በተለይም በቀን ለሚጓዝ መንገደኛ፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው አርሶ አደር ዱላ ይዞ የሚሄደው “ጠላት ስላለው ነው” ለማለትም ሆነ፣ “በየአጋጣሚው ጠብ ስለሚፈጠር ነው” ብሎ ለመናገር ያስቸግራል፡፡ “ጠላትና ጠብ የሚመጣበት አይታወቅም” ተብሎ የሚታሰብ ቢሆን እንኳን ሀቁ ግን ይህ አይደለም፡፡ እውነት-እውነቱን እናውራ ካልን አብዛኛውን ጊዜ፣ አብዛኛው ሰው ጠብ አያጋጥመውም፡፡

በሌላ በኩል የገጠሩ ሰው ዱላ የሚያዘጋጀውና ምን ጊዜም ሊባል በሚችል ሁኔታ ዱላ ከእጁ የማይለየው ለጠብ ካለ ዝግጅት ባይሆንም እንኳን የዱላ አገልግሎት (እቃ ለመሸከም፣ ከብት ለመንዳት፣ ወዘተ) በማይፈለግበት ቦታ ሁሉ ያለ ዱላ መሄድን መጥላቱ እርግጥ ነው፡፡ ዱላ ሳይዙ መሄድ ከነውር የሚቆጠርበትም ሁኔታ መኖሩ ግልፅ ነው፤ ለምሳሌ አንድ ገጠሬ ከተለመደው በማፈንገጥ ዱላ ከእጁ እንዲነጠል ቢያደርግ፣ “እከሌ/እንትና እጁን እንደ ሴት እየወዘወዘ ይሄዳል” በማለት ድርጊቱን የሚያነውሩበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም፡፡ በግጥም (በፋከራ ወይም በቀረርቶ) እስከ መሸንቆጥ ሊደርሱ የሚችሉበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል፡፡ ዱላ ወይም ሺመል የያዘ ሰው፤

“የኔማ እከሌ፣ በዚህ ወረደ

ሺመሉ እንደ’ሳት፣ እየነደደ”

ተብሎ በሚንቆላጰስበት ባህል ውስጥ፣ “እጁን እንደ ሴት እየወዘወዘ” የሚሄድ ወንድ አጥንት በሚነካ የፋከራ ግጥም ቢሸነቆጥ ብዙም ላያስገርም ይችላል፡፡

## ዱላና አምባጓሮ

ዋናው ጥያቄ “በሁሉም ቦታና ምንም የሚያሰጋ ነገር በሌለበት ሁኔታ፣ ‘ቀን-ማታ’ ሳይባል ዱላ መያዝ አስፈላጊ ነው ወይ?” የሚለው ነው፡፡ በአንዳንድ ትንንሽ የገጠር ከተሞች እየሆነ ያለው ምንድነው? አርሶ አደሮች ገበያ ይወጣሉ፣ ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን፡፡ የሚሸጡትን ሸጠው፣ የሚሸምቱትን ሸምተው ወደ ጠላ ቤት ጎራ ይላሉ፡፡ ከመጠጡ ሞቅታ በኋላ አምባጓሮ የሚፈጥሩና በዱላ የሚከታከቱ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ የመጠጡ ሞቅታ ከተነሳ አይቀር፣ አንዳንዶች ደግሞ ወደ ሴት አዳሪዎች “ጎራ” በማለት ለሚስቶቻቸው ሊተርፍ የሚችል “እዳ” (“ኤች. አይ. ቪ.”ን ጨምሮ ሌሎች የአባለ ዘር በሽታዎችን) ይዘው የመሄድ እድላቸውን ያሰፋሉ፡፡

በጋዜጠኛነት ዘመኔ እንደማውቀውና አምና አካባቢ አንድ የፖሊስ መርማሪ እንዳረጋገጠልኝም አብዛኛው አረሶ አደር የሚታሰረው ከነፍስ ግድያ፣ ከድብደባና ከስርቆት ጋር በተገናኘ ወንጀል ነው፡፡ በድብደባና በነፍስ ግድያ ወንጀል ውስጥ ደግሞ ዱላ ትልቁን ሚና መጫወቱ አንድና ሁለት የለውም፤ “ለምን?” ቢሉ አብዛኛው አርሶ አደር የጦር መሳሪያ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# እንግዳችን

## ከጽዳት ሠራተኛ ጀምሮ እስከ ፕሬዚዳንቱ ድረስ ያለው ሕብረተሰብ በአንድ ድምፅ መተንፈስ አለበት፡፡

አቶ ያረጋል ገረመው

**የዚህ ወር እንግዳችን ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ካፈራቸው አንጋፋ ሰራተኞች አንዱ ናቸው፡፡ የህይወትና የስራ ተሞክሯችውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!**



ናይል፡- ስምዎትን፣ የትውልድ ቦታና የልጅነት አስተዳደግዎን ቢገልፁልን?

አቶ ያረጋል፡- ስሜ ያረጋል ገረመው ይባላል፡፡ የትውልድ ቦታ በምዕራብ ጐጃም ዞን በአዲሱ አከፋፈል በጐንጅ ቆለላ ወረዳ በተለይ ይናጭ አቦ በተባለ ቀበሌ በ1948 ዓ.ም ከእናቴ ከወ/ሮ እንይሽ ዓለሙ እና ከአባቴ ከአጋፋሪ ገረመው ጉልማ ተወለድኩ፡፡ ህፃን እያለሁ ከእናት እና አባቴ ጋር በመሆን የመጨረሻ ልጅ ስለነበርኩ በቁልምጫ ተይዤ ስኖር እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ታላቅ ወንድሜ አቶ ይስማው ልመንህ ባሕር ዳር ከተማ ይኖር ስለነበር በ1958 ዓ.ም ላይ ወደ ባሕር ዳር መጥቼ ጥቂት ከቆየሁ በኋላ በ1959 ዓ.ም አፄ ሰርፀ ድንግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንደኛ ክፍል ገብቼ ትምህርቴን ቀጠልኩ፡፡

ናይል፡- የትምህርት ቤት ህይወትዎን አጠር አድርገው ቢገልፁልን?

አቶ ያረጋል፡- የትምህርት ህይወቴ የተጀመረው ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በ1959 ዓ.ም ከ1ኛ ክፍል እስከ 6ኛ ክፍል በዚሁ ትምህርት ቤት ተምሬ አጠናቀቅሁ፡፡

ከሰባት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል አሁን ጣና ሃይቅ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚባለው በዚያን ጊዜ አፄ ሠርፀ ድንግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይባል በነበረው ነው የተማርኩት፡፡ ነገር ግን እኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተማርንበት ወቅት የለውጥ ጊዜ ስለነበር ለትምህርት የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በየክፍለ ሀገር የነበሩ ትምህርት ቤቶች ከለውጡ ጋር በተያያዘ ረብሻዎች በመኖራቸው እየተዘጉ የሚከፈቱበት ጊዜ ቀላል አልነበረም፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች ትምህርት ስለማይፈልጉ በየትኛውም አቅጣጫ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ሳይኖርባቸው ክፍል ብቻ በመቁጠር 12ኛ ክፍል ለማጠናቀቅ የነበራቸው ጥረት ቀላል አልነበረም፡፡ በዚህ መነሻነት ከ9ኛ ክፍል ወደ 10ኛ ክፍል ምንም ሳንፈተን አለፍን፡፡ ከ11ኛ ክፍል ወደ 12ኛ ክፍል ደግሞ ከእድገት በህብረት የተመለሱ ተማሪዎች በዘመቻ ጣቢያቸው ከኢሕአፓ መሥራቾች ጋር ቆይተው የተመለሱና ስለፓርቲው መጠነኛ እውቀት ጨብጠው ስለነበር እነሱም በተራቸው ያልዘመተውን ተማሪ እያሰለጠኑ የተማሪውን ዝንባሌ ከትምህርት ይልቅ ወደ ፖለቲካው እንዲያዘነብል በመደረጉ ረብሻው በመቀጠሉ ወደ 12ኛ ክፍል አሁንም ጥቂት ተምረን ሳንፈተን አለፍን እኔም እንደ ሌሎች ወጣቶች ሁሉ የኢሕአፓ አባል ሆኜ እንደሌሎቹ አባላት የድረሻዬን ስወጣ ቆየሁ፡፡

ከ9ኛ ወደ 10ኛ እና ከ11ኛ ወደ 12ኛ ክፍል ካለምንም ውጤት ማለፋችን በእኔ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል፡፡ ምክንያቱም በአንድ ወቅት ስኮላርሽፕ ቸኮዝሎቫኪያ ጠይቄ ከተቀበሉኝ በኋላ የሁለቱ ክፍሎች በትራንስክርቢቱ ላይ ክፍት ስለነበር ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ፡፡ የኢሕአፓ አባል በመሆን ከሶስት ጊዜ በላይ ታስሬያለሁ፡፡ የምታሰረው በጥርጣሬ ብቻ ስለነበር ከሁለት እና ከሶስት ወር በላይ አልታሰርኩም፡፡

የኮሌጅ ትምህርት የጀመርኩት በ1973 ዓ.ም የባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር ስለነበር በዚሁ ኮሌጅ በማታው መርኃ ግብር በሂሳብ ትምህርት በዲፕሎማ ተመረቅኩ፡፡ እንደአሁኑ የትምህርት ዘርፎች ያልተስፋፉበት ጊዜ በመሆኑ የዲግሪ ትምህርት ለመቀጠል ሳስብ ብቸኛ የነበረው የፔዳጎጂካል ሳይንስ ትምህርት ስለነበር በምርጫ መጣበብ ምክንያት ይህንን ትምህርት ሜጀር በማድረግ አማርኛ ቋንቋ ማይነር አድርጌ እየተማርኩ እያለ በወቅቱ በፔዳጎጂካል ሳይንስ ትምህርት የሚመረቁ ተማሪዎች ሥራ መቀጠር ስላልቻሉ በማይነርነት የምናጠናውን ትምህርት ተጨማሪ ኮርስ ተሰጥቶን እንድንማር በመደረጉ በሁለት ዲግሪ በአማርኛና በፔዳጎጂክስ (ኮምፓዚት ዲግሪ) ተመርቄያለሁ፡፡

ናይል፡- ስለ ትዳር ህይወትዎ እና ቤተሰብዎ ያጫውቱን?

አቶ ያረጋል፡- እኔ ትዳር የመሰረትኩት በጣም ዘግይቼ ነው፡፡ በጊዜው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቀይሬ እሄዳለሁ ብዬ አስብ ስለነበር ለመዘግየቴ ዋና ምክንያት ሆኗል፡፡ ዘግይቼ ማግባቴ ግን አሁን ላይ ሆኜ ሳየው በጣም ጐድቶኛል፡፡ በአሁኑ እድሜዬ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ልጅ ነው ያለኝ፡፡ እሱም ብቸኛ በመሆኑ እና ሃይስኩል ሳይገባ እኔ ጡረታ ስለምወጣ ከልብ ያበሳጫል፡፡ በብዙ መልኩ ተፅዕኖ አሳድሮበታል፡፡ ባለቤቴ ሲ/ር ተዋበች መኮንን ትባላለች፡፡ ሥራዋ አዋላጅ ነርስ ስትሆን የረዥም ጊዜ ልምድ ያላት ሠራተኛ ነች፡፡ እንግዲህ ባለቤቴ፣ አንድ ልጄና እኔ ሆነን የምንኖር ሲሆን የቤቱ ሥራ አስኪያጅ ባለቤቴ ነች፡፡ በመሆኑም የቤቱ ውስጥ አመራር ሙሉ በሙሉ የእሷ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኑሯችን የሚመራው በእቅድ እና በፕሮግራም ነው፡፡ የእኔ ደሞዝ የኤቲኤም ካርድ በእሷ እጅ ስለሆነ የምታወጣው ራሷ ነች፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምን እንደተቀነሰብኝ አላውቀውም እሷ ከራሷ ደመወዝ ጋር ጨምራ ወጪዎችን በአይነት ባይነታቸው ታዘጋጃለች፡፡ የእኔ የኪስ ገንዘብ የሚሰጠኝ ከእሷ ደሞዝ ነው፡፡ ሠራተኞችንን ጨምሮ ሁላችንም የባንክ አካውንት ስላለን በወሩ መጨረሻ አስገብታ ደረሰኙን ለእያንዳንዳችን ታቀርባለች ቀሪው ገንዘብ በእሷ እጅ ሆኖ የቤት ወጪ ይሸፈንበታል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከተማ አብሮኝ የሚወጣ ጓደኛ የለኝም፡፡ ጓደኞቼ ባለቤቴ እና ልጄ ናቸው፡፡ ከተማ መውጣት ስንፈልግ አንነጣጠልም፤ በጋራ ሄደን ተዝናንተን እንመለሳለን፡፡ ከሁለት ሳምንት አንድ ቀን ውጪ እራት እንበላለን፡፡ ይህም በየተራ ግብዣውን እናዘጋጃለን፡፡ ከእሷ እውቅና ውጪ ከተማ ወጥቼ ተዝናንቼ አላውቅም እሷም እንደዚሁ፡፡ ከእንግዶች ጋር የምናመሽ ከሆነ በግልፅ እንደምናመሽ እንነጋገራለን፣ ኑሯችን ሙሉ በሙሉ ግልፅነት የተሞላበት ነው፡፡ መደባበቅ የለም፡፡ እሷ ሳትኖር ከልጇ ጋር ሻይ ብንጠጣ እንኳን መውጣታችንን እናሳውቃለን፡፡

ከሥራ መልስ አብዛኛውን ጊዜ የምናሳልፈው ቤት ውስጥ ነው፡፡ በአቅማችን የምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ቤት ውስጥ አሉ፡፡ ከተማ የሚያስኬድ ነገር የለም፡፡ እንደማንኛውም ባልና ሚስት አልፎ አልፎ ልንነጋገር እንችላለን፡፡ ነገር ግን የተከሰተውን ችግር በመወያየት ተማምነን ችግሮችን እንፈታለን፡፡ ከተማ አላመሽም አንድ ቀን ከሰዎች ጋር ስጫወት አንድ ሰዓት ድረስ አምሽቼ ወደ ቤት ስሄድ እንዴት እስካሁን ቆየህ ብላ ትወቅሰኛለች፡፡ ባጋጣሚ ጓደኛዋ አብራት ስለነበረች እንዴ እንዴት እንደ ደብረብርሃን ሰው በ12 ሰዓት ግባ ትይዋለሽ በማለት አስቃናለች፡፡

ናይል፡- ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ መቼ ተቀላቀሉ? በምን በምን የሥራ ክፍሎች ሰርተዋል?

አቶ ያረጋል፡- ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተቀላቀልኩት በ1971 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ የባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ እየተባለ በሚጠራው ተቋም ነበር፡፡ ስቀጠር የኮሌጁ የንብረት ክፍል ፀሐፊ በመሆን የመነሻ ደመወዜ 153 ብር ነበር፡፡ ነገር ግን ኮሌጁ በትምህርት ሚኒስቴር ሥር ስለነበር የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራሱን በአዲስ እያደራጀ ኮሌጆችን በሥሩ ያደርግ ስለነበር የእኛ ኮሌጅም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር ሆኖ የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲቀጥል ተደረገ፡፡

በንብረት ክፍል ውስጥ የሚሠራባቸው ደረሰኞች የወጪና ገቢ የተለያዩ ቅፆች የገንዘብ ሚኒስቴር ስለነበሩ በእነርሱ ፈንታ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የአሠራር ስልት መከተል እንዲቻል እኔ ወደ አዲስ አበባ ተልኬ እንዳጠናና ቅፆች እንዲለወጡ ተደረገ፡፡ በወቅቱ ኮምፒውተር አዲስ ስለነበር ለተጨማሪ ጥናት ቦሌ አየር መንገድ እንዳጠና ተልኬ ኮምፒውተር ያየሁት በዚያን ወቅት ነበር፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናትና ስልጠና ከተመለስኩ በኋላ አሁን ዩኒቨርሲቲው የሚጠቀምባቸውን የንብረት ክፍል ቅፆች እና የተለያዩ ሰነዶች አሠራር ያዘጋጀሁት እኔ ነኝ፡፡

⇨

# እንግዳችን ...

ብዙ ሳልቆይ የንብረት ክፍል ተጠባባቂ ኃላፊ በመሆን ተመድቤ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ በሠራተኛ አስተዳደር የስታትስቲክስ ሠራተኛ ሆኜ ለአንድ አመት ያክል አገልግያለሁ። ከዚያ ቀጥዬ የእቃ ግዥ ክፍል ሠራተኛ በመሆን ሠርቻለሁ። በተለያዩ ክፍሎች በመሥራቴ ያካበትኩት ልምድ የጠቀመኝ ይመስለኛል። የኮሌጁ የገንዘብ ቤት ኃላፊ በመሆን ሠርቻለሁ። በኮሌጁ ውስጥ የሥራ እድገት ለማግኘት በጣም አዝጋሚ ነበር ነገር ግን እኔ በወቅቱ የሥራ ጥራት ይሆን እድል አላውቅም ቶሎ ቶሎ የመዛወርና የማደግ አጋጣሚውን አገኝ ነበር ከገንዘብ ቤት ኃላፊነት ተዛውሬ የኮሌጁ የንብረትና እቃ ማደራጃ ክፍል ኃላፊ ሆኘ ተመደብኩ። ደመወዜም በዚያው ልክ ይጨምር ነበር። ሶስት ዓመታት ያክል በዚህ የኃላፊነት ሥራ ሥሰራ እንደቆየሁ የኮሌጁ የጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ በመሆን ተመድቤ ሠርቻለሁ።

በ1992 ዓ.ም የፖሊቴክኒክ ተቋም እና ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ አንድ ላይ በመሆን ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሲመሰረት የተለያዩ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ መዋቅሮች ተሠርተው ነበር። በዚህ መዋቅር መሠረት እኔም የዩኒቨርሲቲው የቴክኒክና ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን ተመድቤ ሠርቻለሁ። በዚህ በኋላ ዩኒቨርሲቲው እንደገና አዲስ መዋቅር የሰራ በመሆኑ እኔም የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ መቆጣጠሪያና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የተመሰረተ በመሆኑ ብቻዬን አዲሱ ቢሮ ውስጥ አስተባባሪ ተላላኪ ጸሐፊ ሌሎችንም በመሆን ክፍሉ አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጌያለሁ።

ዩኒቨርሲቲው መዋቅር በየጊዜው እየሰራ ሠራተኛውን ባያረካውም አሁንም እንደገና አዲስ መዋቅር የተሰራ ስለሆነ ከኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በቢሮ ደረጃ ተዋቅሮ ለመሥራት አዲስ በተከፈተው የዩኒቨርሲቲው የባሕል ማዕከል ኃላፊ ሆኜ ተመድቤ አገልግያለሁ።

ናይል፡- በሥራ ዓለም ሲኖሩ አሳዛኝም ሆነ አስደሳች ገጠመኝ ካለዎት ቢያካፍሉን?

አቶ ያረጋል፡- በሥራ ዓለም የቆየሁት ረዥም ጊዜ ስለሆነ አስደሳችም ሆነ አሳዛኝ ነገር መግጠሙ አይቀርም። በዚህ መሰረት በመጀመሪያ አስደሳቹን ልግለፅው፤ እኔ ስቀጠር ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ ይባል ነበር። የታሪክ እድገት ነው እና ይህ ኮሌጅ እኔ በሥራ ላይ እያለሁ ወደ ዩኒቨርሲቲ ማደጉ ታላቅ ደስታ ሰጥቶኛል። በኮሌጃችን ውስጥ አንድ እና ሁለት ሺህ ተማሪ ተቀብለን ስናስተምር የቆየን ሰዎች በአንድ ጊዜ ስምንት ሺ ተማሪዎችን ቆሞ ማስመረቅ አገሩንና አካባቢውን ለሚወድ ሰው ታላቅ ደስታ ነው።

ሌላው እኔ ኤች አይ ቪ ኤድስ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተመድቤ ስሄድ ለቢሮው ብቸኛው ሠራተኛ ነበርኩ። ይህ ቢሮ አሁን ወደ ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት ማደጉ እና ከ12 በላይ ሠራተኞች ተመድበው ይህንን ቀሳፊ በሽታ በጋራ ሲከላከሉ በማየቴ የሠራሁት ሥራ ፍሬያማ መሆኑን ያስገነዝበኛል። በዚሁ ክፍል እያለሁ የዩኒቨርሲቲውን ሕብረተሰብ እርዳታ ጠይቄ ከወር ደመወዛቸው እየተቀነሰ የሚከፈለው ገንዘብ 5 ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ ኢድስ ያጡ ሕፃናትን እያስተማርን በመሆኑ ይህም ሌላ ደስታ ፈጥሮልኛል። በመጨረሻም የምገልፀው ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በማህበር እንዲደራጁ ያደረኩት ሥራ ያረካኛል። እነዚህ ሠራተኞች መጀመሪያ ላይ ራሳቸውን አጋልጠው ሲወጡ መድሎና መገለል ያደረሰባቸው ቢሆንም ባሳዩት ቆራጥነት ማህበሩ ሕይወት ዘርቶ አሁን ካሉበት ደረጃ እንዲደርስ አድርገዋል። በዩኒቨርሲቲው በኩል ብዙ እገዛ ባይደረግላቸውም ፕሮጀክት ቀርጨ አንድ ፎቶ ኮፒ ማሽን በማግኘታችን የቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በለገሰላቸው እንደ ኮንቲነር አባላት ገንዘብ አዋጥተው ሱቅ ከተከፈተ በኋላ ፎቶ ኮፒ ማሽኑም ሌላ የገቢ ማስገኛ ሆኖ በአሁኑ ሰዓት አባላቱ የተሻለ ገንዘብ አግኝተው በሌሎች ኮሌጆች ውስጥ ቅርንጫፍ ከፍተው እየሰሩ ማየቴ ከተሰራ አስገራሚ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተገንዝቤያለሁ። ይህም ከፍተኛ ደስታን ፈጥሮልኛል።

በቆየሁባቸው ጊዜያት አሳዛኝ ነገር ያየሁት በእኔ በራሴ ላይ ነበር። ዩኒቨርሲቲው መዋቅር ለመሥራት አንደኛ ነው ነገር ግን ፍትሃዊ የሆነ ድልድል ማድረግ የመጨረሻ ደመኛው ነው። ወገናዊነት በጣም ያሸንፈዋል። እኔ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ ጽ/ቤት መሥራች እና ሠራተኛ ሆኘ ሳገለግል በመቆየቴ የነበረኝ የሥራ አፈፃፀም በጣም ጥሩ በመሆኑ በኮከብ ሠራተኛነት ሁለት ጊዜ ከፕሬዚዳንቶቹ በራሳቸው ፊርማ የተመሰከረለት ሰርተፍኬት ተሰጠኝ። እኔም ይህ የምሥክር ወረቀት ለተሻለ ሥራ እንደማያነሳሳኝ ተስፋ በማድረግ እየሰራሁ እያለ የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ (አገልግሎት) እያለኝ ከወጡት የዳይሬክቶሬት ቦታዎች ውስጥ አንዱን አገኛለሁ ብዬ ስጠብቅ ቆየሁ። በመጨረሻ እንኳንና ዳይሬክተር ልሆን ቀርቶ ከነበርኩበት ደረጃ እርከን ዝቅ ብዬ ተመደብኩ። ይህ መጥፎ ውሳኔና ለታታሪ ሠራተኛ የሚደረግ ተግባር አልነበረም። ይህ ጉዳይ በአእምሮዬ ላይ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ አልፏል። ምናልባት እኔ በሚዲያ ይህንን ሃሳብ ማስተላለፍ በመቻሌ እድለኛ ነኝ። የዚህ አይነት ችግር ደርሶባቸው እስካሁን የሚያለቅሱ ሠራተኞች አሉ።

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 2017 አፍሪካ ከሚገኙ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ አስቀምጧል። ራዕዩን ለማሳካት ምን መሠራት አለበት ይላሉ?

አቶ ያረጋል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 አፍሪካ ከሚገኙ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን እየሰራ ይገኛል። ይህ መፈክር ተሰቅሎ መነበብ የጀመረው ከሶስት አመት በፊት ይመስለኛል። ይህንን እድል ብናገኝ ሁላችንም ደስታችን ወሰን የለውም። ነገር ግን ወደዚህ ግብ ለመሄድ መሠረት እየጣልን አይመስለኝም። ለዚህ ውጤት መሳካት የላይኛው አመራር ብቻውን የሚያመጣው ነገር የለውም። ከጽዳት ሠራተኛ ጀምሮ እስከ ፕሬዚዳንቱ ድረስ ያለው ሕብረተሰብ በአንድ ድምፅ መተንፈስ አለበት። መንገዱን ለመጥረግ ግቡ ወዳለበት አቅጣጫ ሁሉም ባለው አቅም መራመድ አለበት።

ነገር ግን ይህን መንገድ በጋራ ለመሄድ የሚያስችል ንድፍ የተነደፈ አይመስለኝም። በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንትና በሠራተኛው ላይ አለመግባባት ሊኖር ይችላል። ከታሰበው ግብ ለመድረስ ማኔጀመንቱ ቆም ብሎ ማሰብ አለበት። ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የጋራ ማድረግ አለበት። መምህሩ፣ ሠራተኛውና ተማሪው ዩኒቨርሲቲውን ለማሳደግ የእኛ ነው ብሎ መነሳት አለበት። ወደ ሕብረተሰቡ ዘልቆ መሥራት አለበት። የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚል ምልክት የተፃፈበት መኪና ሲታይ የጣት መቀሰሪያ ሆኗል። ይህንን መንፈስ ለመቀየር ዩኒቨርሲቲው ወደ ሕብረተሰቡ ሰርፆ መግባት አለበት። በአፍሪካ ካሉት የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አሥረኛ ለመሆን በዩኒቨርሲቲው ሊሰሩ የሚገባቸው በርካታ መሥፈርቶች አሉ። እነዚህን ጉዳዮች በጥልቀት መሥራት ነው። በነዚህ ሥራዎች ላይ የሁሉም ክንድ የሁሉም አሻራ ሊያርፍባቸው ይገባል። ችግሮች የጋራ በትግል የተገኙ ውጤቶች የጋራ ሠራተኛው ሥራውን የኔ ሥራ ነው ብሎ ከሠራ ከዚህ ውጤት በላይ ማምጣት ይቻላል።

ናይል፡- ለዩኒቨርሲቲው ይህ ይጠቅመዋል የሚሉት አስተያየት ካለዎት ቢገልፁልን?

አቶ ያረጋል፡- ለዩኒቨርሲቲው ማደግ ይበጃል ብዬ የማስበው በመጀመሪያ በሠራተኛው እና በማኔጅመንቱ መካከል ቅራኔ ካለ መፈታት አለበት። የበላይ አመራር አካላት ሠራተኛውን በአንድ አይን መመልከት አለባቸው። አሰራሩ ግልፀኝነት የሰፈነበት መሆን አለበት። አንዳንድ ክፍል በራስ የመተማመን ስሜት አይታይም። በሞግዚትነት የሚመሩ ክፍሎች አሉ። እነዚህ ክፍሎችን ደንብ እና ሥርዓትን ተከትለው ራሳቸውን ችለው መሥራት ይኖርባቸዋል። በበላይ አመራር አካላት የሚወሰኑ ውሳኔዎች ሲዋዥቁ ይስተዋላል። ሠራተኛ አዲስ መዋቅር ተሰርቶ ተመድበው ሥራ ጀምረው ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ እንደገና የመዋቅሩን መሥፈርት አታሟሉም ተብለው ከእርከን እየወረዱ የተመደቡ ሠራተኞች ብዙዎች ናቸው።

ይህ አሠራር መቆም አለበት። ሠራተኞች ከዚህ ቀደም ያገኙት የነበረው ጥቅማጥቅም ተቋርጧል። ይህ ጉዳይ እንደገና ታይቶ ሠራተኛው የሚደጐምበት መንገድ ቢፈለግ፣ መምህራን በቤት እጦትና በመልካም አስተዳደር ችግር ምክንያት እያሳበቡ ዩኒቨርሲቲው እየለቀቁ የሚሄዱት ቀላል አይደለምና ይህን ማስተካከል፣ ብዙ መምህራን ሪሰርች ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጐት አላቸው። ነገር ግን በፋይናንስ አካባቢ የሚታየው የአሰራር ችግር አንገፍግፏቸው ሪሰርችን ርግፍ አድርገው የተው መምህራን አሉ። ካለ ሪሰርች ዩኒቨርሲቲውን በበጐ ጐኑ ሊያስጠራው የሚችል ነገር አይኖርም። ስለዚህ የሚመለከተው አካል ወደ ችግሩ ዘልቆ በመግባት ችግሩን ነቅሶ አውጥቶ መፍትሄ መስጠት ይኖርበታል።

ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ክፍሎች በአመራርነት ሰርተዋል። ይህ ልምድ ቢያካፍሉን?

አቶ ያረጋል፡- በኮሌጆችም ሆነ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሃላፊነት ቦታዎች ሠርቻለሁ። የንብረት እቃ ማደራጃ ክፍል ኃላፊ ሆኘ በሠራሁበት ወቅት ንብረቶች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው መመሪያዎችን አዘጋጀች ነበርን። ቋሚ ንብረቶች አሁን በማርከር የሚፃፈው ጽሁፍ ለእቃውም ሆነ ለእይታ ስለማይመች ከብረት የተቀረፀች ኮድና ቁጥር መያዝ የምትችል መለያ ለጥፈን መገልገል እንችል ነበር። አሁን የለም ወደፊት በዚህ መልኩ ቢሰራ መልካም ነው።

ኤች አይ ቪ ኢድስ መከላከል እና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በሽታው ከሚያስከትለው ችግር አንፃር ብዙ መሥራት ይጠበቅበታል። ከብዙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥረናል ስለዚህ ይህ ግንኙነት ወደፊት የበለጠ መጠናከር አለበት። ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በተደረገው በጋራ የመሥራት ስምምነት ዩኒቨርሲቲያችንን ወክየ በመሄድ ፖሊሲ ቀርፀን ከፀደቀ በኋላ በሁሉም በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሠራበት በመደረጉ በተለይ በተማሪዎች በኩል ሥራው ተደራሽ እንዲሆን ጠንክሮ መሥራት ያሻል። ከዚህ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ አስቀርፀን ወደ ተግባር የተገባ በመሆኑ ይህንንም በቀጣይነት የሚሰራበትን መንገድ መቀየስ ያሻል።

ኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ ያለባቸው ማህበር በግቢያችን ተቋቁሞ በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ቫይረሱ ያለባቸው ሌሎች አካላት ወደ ማህበሩ እንዲቀላቀሉ እና በጋራ የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው። ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ ኤድስ ያጡ ሕፃናትን መምህራንና ሠራተኞች በሚያዋጡት ገንዘብ እየተረዱ በመማር ላይ ይገኛሉ። ዩኒቨርሲቲው ካለው የሰው ኃይል እና አቅም አንፃር ሲታይ 5 ሰው በቂ አይደለም። ሕብረተሰቡ ገንዘብ ለማዋጣት ችግር የለበትም። ትልቁ ሥራ ማስተባበር እና መከታተል ነው። ስለዚህ የዩኒቨርሲቲውን ሕብረተሰብ አስተባብሮ የተረጅ ሕፃናትን ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ አስፈላጊ ይመስለኛል። ይህን በማድረጋችን በርካታ ሕፃናትን ከሞትና ከመፈናቀል መታደግ እንችላለን።

ናይል፡- ካለዎት የሥራ ልምድ የዩኒቨርሲቲውን አመራር ሂደት እንዴት ያዩታል?

አቶ ያረጋል፡- የዩኒቨርሲቲው የአመራር ሂደትን በተመለከተ የምናገረው፣ በአሁኑ ጊዜ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ነው። በዚህ ምክንያት በርካታ በጀት ተመድቦለታል። በርካታ ተማሪዎችን፣

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# ጉድ ሰራችኝ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

ማርታና ካሌብ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ማርታ በትምህርቷ ጉብዝና ልበ ሙሉ ሴት ናት፡፡ ካሌብ በትምህርቱ መካከለኛ የሚባል አይነት ነው፡፡ ወንዳ ወንድነቱና መልኩ ብዙ ሴቶችን ማማለል ቢችልም ማርታ ግን አማላይነቱ ልብ ብለው አታውቅም፡፡ (ታሪኩ የሚጀምረው ካሌብ እንዴት አድርጐ ማርታን እንደሚያጠምድ ከጓደኞቹ ከቢኒያምና አቢ ጋር ሲመካከር ነው፡፡) ዘመኑ ያለንበት፣ ጊዜው ቀን አንደኛው ወሰነ ትምህርት ቦታው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቢኒያም፡- ካሌብ ግን ለምን አትቀርብህም? ብዙ ሴቶችን የማፍዘዝና የማጥመድ ችሎታ አለህ፡፡ ከዚህች ፉንጋ ጋር ምን ታደርጋለህ?

ካሌብ፡- ማንም ሴት እኔን እንቢ ብላ አታውቅም፡፡ ማርታ ምን ስለሆነችና በምን ስለተለየች እንቢ ትለኛለች?

አቢ፡- ምናልባት ጎበዝና ልብ ሙሉ ስለሆነች ይሆናላ የተማረክላት፡፡

ካሌብ፡- የተማረክላት መማረክ እኔ ለሴት… በጣም ትገርማለህ? ሴቶች እኮ የእኔ አሻንጉሊቶች ፣የኔ ፊልሞች ፣ የኔ መዝናኛዎች ናቸው፡፡

ቢኒያም :- ማርታ ግን አይደለችም ፡፡ ወንድ ትሆን እንዴ?

አቢ :- ያስብላል ፤ ቀላል አይደለችም ፤ አትበገርም ፡፡

ካሌብ፡- ባክህ አንዴ ከንፈሯን እስክስማት ነው፡፡ የሴትን ስስ ብልት ታውቃለህ? ከንፈራቸው የመጀመሪያ፣ ቀጥሎ ደግሞ ጡታቸው ነው፡፡ አንዴ ከንፈራቸው ከተሳመ መቅለጥ ይጀምራሉ፤ ሌላውንም ከመሰጠት ወደ ኋላ አይሉም ፡፡

ቢኒያም :- ማን ትሪንስፖርት ሆና ከከንፈሯ ላይ ያድርስህ ታዲያ?

ካሌብ፡- ዝም በል አንተ ደግሞ በማጠምድበት መንገድ አጠምዳታለሁ፡፡ ከተሸነፈች በኃላ ግን አልፈልጋትም፡፡

አቢ :- ምን? በጣም የሚያስጠላኝ ባህሪህ ይህ ነው? ካልፈለካት ለምን?

ካሌብ፡- እምቢ የምትለኝ ሴት እልህ ስለምታሲዘኝና ከነእልሄ መቀመጥ ስለማልችል፡፡

ቢኒያም፡- ይህ ጥሩ ባህሪ አይመስለኝም፡፡ ብተዋት ጥሩ ነው፡፡ በቃ ብዙ የሴት ጓደኞች አሉህ፡፡ ከፈለክም መጨመር ትችላለህ፡፡ ፍላጐት የሌላትን ሴት ግን አትጫናት፡፡

ካሌብ፡- ያቺ ጓደኛዋ ማን ናት? ሀና ካንተ ጋር ትቀራረባለች አይደል?

ቢኒያም፡- ሀና? አዎ! ምነው?

ካሌብ፡- በቃ “do me a favor” (ሁለት እጆቹን አፉንጫው ላይ አሳርፎ) እሷ ስለማሪታ ሁሉን ነገር አጣርታ ትንገርህ፡፡

ቢኒያም፡- ለምን?

ካሌብ፡- በደካማ ጐኗ ለመግባት እንዲመቸኝ፡፡

ቢኒያም፡- የምትበገር አይመስለኝም ለጓደኝነታችን ስል አደርገዋለሁ፡፡፡

አቢ፡- ጨዋታው አልጣመኝም፡፡ ከዚህ ነገር የለሁበትም፡፡

---------------//--------------

ሀና እና ማርታ የተማሪዎች መዝናኛ ቁጭ ብለዋል፡፡ ካሌብና ቢኒያም ድንገት የተገናኙ በሚመስል አኳኋን መጥተው ሰላምታ አቀረቡላቸውና፤ አብረዋቸው ተቀመጡ፡፡

ሀና፡- እንዴት ናችሁ?

ካሌብ፡- ሰላም ነን እናንተስ /ማርታን ሰረቅ አድርጐ እያያት/

ማርታ፡- ደህና ነን፡፡

ቢኒያም፡- ሀና አንዴ ብቻሽን ፈልጌሽ ነበር፡፡ (ወደ ማርታ ዞሮ) ማርታ ቅር ካላለሽ ለብቻየ ላነጋግራት?

ማርታ፡- ከቆያችሁ ግን እኔ ወደ ላይበራሪ እሄደለሁ?

ሀና፡- እንዴ አብረን እንሄዳለን፡፡ ምንድን ነው? ጉዳዩ ብዙ ያቆያል?

ቢኒያም፡- ኧረ የሆነ ነገር ልጠይቅሽ ስለፈለኩ ነው ቶሎ እንመለሳለን ካሌብ እስከዛ ማርታን አጫውታት (እየጠቀሰው ሀናን አቅፏት ይወጣል)፡፡

ካሌብ፡- አትቆዩ እኔም የምሄድበት አለኝ ፡፡

ሀና እና ቢኒያም ተነስተው ሲሄዱ ካሌብና ማርታ ከተወሰነ ጊዜ በዝምታ ቆዩ

ካሌብ፡- ላይበራሪ የምትገቢው ፈተና ደረሰ እንዴ?

ማረታ፡- አይ ፈተና ስለደረሰ ሳይሆን ማንበብ ስለምወድና በፈተና ሰዓትም መጨናነቅ ስለማልፈልግ ሁሌም ላይብረሪ እገባለሁ፡፡

ካሌብ፡- ደስ ይላል፡፡ እኔ ፈተና ካልደረሰ ማንበብ አልወድም፡፡ የማንበብ ሙድ የሚመጣልኝ ፈተና ሲደርስ ብቻ ነው፡፡

ማርታ፡- ጥሩ ልምድ ግን አይመስለኝም፡፡

ካሌብ፡- እንዴት?

ማርታ፡- ዛሬ መነበብ ያለበት ለነገ ሲባል የሚነበበው ነገር ይበዛል፡፡ በፈተና ወቅት የመጨናነቅና የመረበሽ ስሜት ይፈጥራል፣ እህ… ውጤታማም የሚያደርግ አይመስለኝም፡፡

ካሌብ፡- እሱን ነው የምልሽ እኔ በቃ ስጨናነቅ በደንብ አጠናለሁ፡፡ ዘና ባለ ሁኔታ ውስጥ ስሆን መዝናናት እንጂ ማጥናት ይደብረኛል፡፡ እየተጨነኩ ያጠናሁት አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ሆኖልኛል፡፡ ብቻ ምን አለፉሽ አጥንቼ አላውቅም፡፡ (ወደ ላይ እየተመለከተ) እግዚአብሔር ይመስገን እስካሁን አልወደኩም፡፡

ማርታ፡- አካሄድህ ካዋጣህ ጥሩ ነው፡፡

ካሌብ፡- ይልቅ አንቺ ሁልጊዜ ስትቸክይ ቀን ከሌት ስታጠኝ አይሰለችሽም?

ማርታ፡- የመጣሁት ልማር አይደል እንዴ ለምን ይሰለቸኛል?

ካሌብ፡- እሱስ እውነትሽ ነው ግን አለ አይደል ትንሽ ዘና ማለት የሚያስፈልግ አይመስልሽም?

ማርታ፡- እንዴት ያለ ዘና ማለት?

ካሌብ፡- ወጣ ማለት፣ ሌላውን አለም መመልከት፣ ዘና ማለት፣ ፈታ ማለት… ወጣትነትን ማጣጣም፣ ከየጣፋጩ መቅመስ … አያስፈልግም ትያለሽ?

ማርታ፡- የት ያመልጠኛል ብለህ ነው ትምህርቴን ስጨርስ እደርስበታለሁ፡፡

ካሌብ፡- አይ ትምህርት ላይ እያለሽ እኮ ህይወትን ማጣጣም አለብሽ፡፡

ማርታ፡- እሱን እማ እያጣጣምኩ ነው!

ካሌብ፡- ፍቅረኛ አለሽ እንዴ?

ማርታ፡- እንዴ? እንዴት? ለምን ጠየከኝ?

ካሌብ፡- አይ “ላይፍን” እያጣጣምኩ ነው ስትይኝ ጊዜ ነዋ?

ማርታ፡- ላይፍ ላንተ ከፍቅረኛ ጋር ያለ ብቻ ነው?

ካሌብ፡- ታዲያ የቱን ነው የምትይኝ? አለሽ? ወይንስ የለሽም?

ማርታ፡- ለኔ በካምፖስ ላይፍ ትምህርት ነው፡፡

ካሌብ፡- ኡፍ! ፍቅረኛ ከሌለሽ በጣም ደስ ይላል (ወደ ጎን ዞሮ ለሷ በማይሰማ መልኩ) አለኝ ብትይኝ ምን ይውጠኝ ነበር፡፡

ማርታ፡- ምኑ ነው ያስደሰተህ?

ካሌብ፡- እውነቱን ልነገርሽ ማርታ ተሸንፌያለሁ፡፡ ድብን ያለ ፍቅር ካንቺ ይዞኛል፡፡

ማርታ፡- በል አታስቀኝ በቅጡ ሳታውቀኝ ፍቅር ያዘኝ ልትለኝ ነው?

ካሌብ፡- ፍቅር መቼ በትውውቅ ሆነና አየሁሽ ወደድኩሽ በቃ አስቢበትና መልስሽን ንገሪኝ፡፡

ማርታ፡- የማስበው ነገር የለኝም፡፡ ፍቅር ቀልድ ነው እንዴ? ድንገት ተነስተህ ፍቅር ያዘኝ ትለኛለህ? ከመንገደኛ ጋር ነው እንዴ ፍቅር የሚይዝህ?

ካሌብ፡- ፍቅር መንገደኛ አይል ቤተኛ በዕቅድ እኮ የሚደረግ አይደለም ካየሁሽና ከወደድኩሽ ቆይቻለሁ፡፡ አጋጣሚውን ስጠብቅ ዛሬ አገኘሁሽ ነገርኩሽ፡፡

ማርታ፡- በጣም ይቅርታ አሁን ለፍቅር ቦታ የለኝም፡፡

ካሌብ፡- ትንሽ ጥግ ብቻ ነው የምፈልገው ብዙ አላስቸግርሽም፡፡ በሰጠሽኝ ቦታ ፀባዬን አሳምሬ እጥፍጥፍ ብዬ እቀመጣለሁ፡፡

ማርታ፡- የምንግባባ መስሎኝ ነበር፡፡ ይቅርታ ላይበራሪ ልሄድ ነው፡፡ /ማርታ ካሌብን ከተቀመጠበት ትታው ትሄደለች፡፡ ካሌብ በብስጭት ፀጉሩን ይነጫል፡፡/

ካሌብ፡- ቆሞ ወደሄደችበት አቅጣጫ እየተመለከተ እኮ ምን ስለሆንሽ ሴት እኮ ነሽ? ባንቺ ቤት ኮስታራ መሆንሽ ነው፡፡ እኔ ካሌብ የፍቅር ጀግና ነኝ፡፡ ማንም ሴት እንቢ አትለኝም፣ አሳይሽለሁ፡፡

---------------//--------------

አቢ እና ቢንያም ስለ ካሌብ እየተጨነቁ ያወራሉ፡፡

አቢ፡- በእናትህ ካሌብ እኮ በጣም ችግር ውስጥ ነው፡፡ የቀልድ የጀመረው የምር ሆኖበታል፡፡ ማርታን አፍቅሯታል፡፡

ቢኒያም፡- በተለይ ትናንትና ሌሊት ዶርም ስሟን እየጠራ ሲቃዥ ነበር:: ነገሩ “serious” እንደሆነ ነው የተረዳሁት፡፡

አቢ፡- እንዴት ልንረዳው እንችላለን?

ቢኒያም፡- እኔ ምን አውቃለሁ፡፡ እናናግራት እንዴ?

አቢ፡- ምን ብለን?

ቢኒያም፡- ‹‹እሺ በይው በፍቅርሽ እየተጨነቀ›› ነው ብለን ነዋ፡፡

አቢ፡- ካሌብ ይስማማል፡፡

ቢኒያም፡- ባይስማማ ምን አማራጭ አለው፡፡ ሁለት ሶስቴ አግኝቶ አነጋግሯቷል፡፡ ስልኳን አፈላልጐ ደውሎ የፍቅር ዜማውን ለቆላታል፡፡

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ዱላና ዱለኝነት ...

ከገጽ 7 የዞረ

የለውምና፡፡ ስለዚህ ዱላ በተለይም ዱለኝነት የአርሶ አደሩን ህይወት ለመለወጥ በሚደረገው ትግል ውስጥ አንዱና ዋነኛው መሰናክል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ዱላ ከአርሶ አደሮች እጅ አለመለየቱ ጠብና አምባጓሮ እንዲነሳ ከፍተኛ ግፊት ሊፈጥር እንደሚችል ያጫወትኩት አንድ የባህር ዳር ከተማ ፖሊስ በምሳሌነት የነገረኝ የወረታ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤትን ነው፡፡ ወደ ከተማዋ ለገበያ ከሚመጡ አርሶ አደሮች በተለያየ ጊዜ ፖሊስ የሰበሰበው ዱላ የሰው ቁመት ያህል ተቆልሎ ከጽ/ቤቱ ደጅ በአንድ ወቅት ማየቱን ነገረኝ፡፡

በነገራችን ላይ ጠጥተው የሚሰክሩና በዱላ የሚደባደቡ አርሶ አደሮች ከሚበዙባቸው ቦታዎች አንዱ የወረታ ከተማና አካባቢ ነው፡፡ ባለፈው አመት ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህራን ጋር በመሆን ከሁለት ባልደረቦቼ ጋር ለምንሰራው ጥናት በበወረታ ዙሪያ ወደሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ለመሄድ በተዘጋጀንበት ወቅት፣ የአንዱ ባልደረባችን ባለቤት ወደስፍራው ከሰአት በኋላ በተለይም ቅዳሜ ቀን መሄድ እንደሌለብን እንደ መከረችው የነገረንን አስታውሳለሁ፡፡ ምክንያቷ ደግሞ በስራ አጋጣሚ አካባቢውን እንደምታውቀው፣ አንዳንድ አርሶ አደሮች ከገበያ መልስ ጠጥተው በመምጣት አምባጓሮ የሚፈጥሩ መሆናቸው ነው፡፡

## የዱለኝነት "ባህል"

እዚህ ላይ ልንተማመንበት የሚገባ ነጥብ አርሶ አደሮች ባብዛኛው ቦታና ሁኔታ ዱላ የሚይዙት፣ ዱላ የመያዝ ባህል ስላላቸው ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ ዱላ የመያዝ ብቻ ሳይሆን የዱለኝነትም ባህል ስላለን ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የሁለቱ ባህሎች ድድርነት ወይም ጥንካሬ እኩል ነው ማለት አይደለም፡፡ የሆነ ሆኖ "ባጋጣሚ ሰው ጋር ብጣላ፣ ካንዱ ጋር ብጋጭ" በሚል ሰበብ አርሶ አደሮች ዱላ ከእጃቸው እንደማይለዩ ብዙ አመላካቾች አሉ፡፡ አንዱ ዋና ማስረጃ የዱላው የዝግጅት ሁኔታ ነው፡፡ ከተገኘው ዛፍ ሁሉ ዱላ አይዘጋጅም፤ እንደየ አካባቢው ሁኔታ ከዛፍም ዛፍ ይመረጣል፡፡ ለምሳሌ የክትክታ፣ የወይራ፣ የቀሮሬሳ… ዛፎች ለዱላ ወይም ለበትር ተመራጭ ናቸው፤ "ለምን?" ቢሉ፣ እነዚህ የዛፍ አይነቶች በጣም ጠንካራና በቀላሉ የማይሰበሩ ናቸውና፡፡ ለዚህስ አይደል፤

"ኧረ አዬዋ እከሌ፣ የነጭ ላም እበት

ክትክታ ተይዞ፣ ምን ሊደረግበት፡፡

በቀጋ ሽመል፣ ብሸነቁጠው

አሬራው ወጣ፣ ያልተላመጠው" መባሉ፡፡

የዱላ ዝግጅት በዛፉ አይነት ምርጫ ላይ ብቻ አያቆምም፡፡ ዱላው ሲቆረጥ፤ "ቁመናው" መለል ብሎ የወጣ ሆኖ፣ ከስሩ በኩል የህፃን ልጅ ጭብጥ የሚያክል እብጠት ወይም ውፍረት ቢኖረው ተመራጭ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ካልተገኘ ወደ ባህላዊ የብረታ ብረት ባለሙያ ዘንድ በመውሰድ ጅንፎ ይደረግለታል - ማለትም ከዱላው የታችኛው አካል ላይ በመጠኑ ቀጠን ብሎ ጠፍጠፍ ያለ ብረት ይጠመጠምበታል፡፡ አንዳንድ ገበሬዎች ዱላውን በእሳት የሚለበልቡበትም አጋጣሚ አለ - ተጨማሪ ጥንካሬ እንዲያገኝ፣ "እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተነ" ባይባልም፡፡ ዱላው ጅንፎ ተደረገለትም አልተደረገለትም፣ የከብት ጅራት ቆዳ (ከብት ሲታረድ፣ የጅራቱ ቆዳ ሳይሰነጠቅ/ሳይቀደድ ተሸልቅቆ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ) እንዲለብስ የሚደረግበትም አጋጣሚ አለ፡፡ ዱላው የቀርቀሀ ከዘራ ከሆነ ደግሞ ከጅንፎው በተጨማሪ የምግብ ዘይት እንዲጠጣ ይደረጋል - ይበልጥ ጠንካራ፣ ሲመቱበት የሚለመጥ እንጂ የማይሰበር እንዲሆን፡፡ ይህ ሁሉ ዝግጅት ዱላው በተፈጥሮው ካለው ጥንካሬ ላይ ተጨማሪ ጥንካሬ ለመስጠት መሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡ በክልላችን አንዳንድ ቦታዎች የቀርቀሀ ከዘራን ጨምሮ ዱላ ወይም በትር ገበያ ላይ የሚሸጥ ሸቀጥ መሆኑም ተጨማሪ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

አብዛኛው አርሶ አደር ተጨባጭ የሆነ ስጋት በሌለበት ሁኔታ የዱላ ዝግጅት ማደረጉ አያጠያይቅም፡፡ ዱላ ይዞ መጓዝ ከደም-ስሩ ጋር ተዋህዷል፤ ባጭሩ ባህሉ ሆኗል፡፡ አብዛኛው አርሶ አደር "ያለ ጠብና አምባጓሩ ህይወቱን ያሳልፉል" የሚል መላ ምት ብናስቀምጥ እንኳን፣ ብዙዎቹ አርሶ አደሮች "ሊመጣ ይችላል" ብለው በህሊናቸው ለሳሉት ጠብና አምባጓሩ ተዘጋጅተው ህይወታቸውን እንደሚያሳልፉ ከላይ ያለው የዱላ ዝግጅት ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ይህን አይነቱን አስተሳሰብ የሚወልዱና ኮትኩተው የሚያሳድጉ የስነ ቃል ትውፊቶችም አሉን፤

""እባክሽ እናቴ፣ ውለጅ መንታ-መንታ

ቀኝ እጄ ሲመክት፣ ግራ'ጄ ተመታ፡፡

"በጠራው ሰማይ ላይ፣ ይጓዛል ዳመና

አባት ብትር እንጂ፣ አይሰጥም ልቦና፡፡

"እንኳን በጠመንጃ፣ ጥይት በጎረሰው

በብትር ያስቀራል፣ ወኔ ያለበት ሰው፡፡"

"ምንም ጥርጣሬ የሚባል ነገር የለም፤ ጠብና አምባጓሮ እዚህም-እዚያም እንዳፈር ሞልቷል" ከተባለም እንኳ አርሶ አደሩ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥመው፣ የአካልም ሆነ የህይወት ጉዳት ከመድረሱ በፊት "ለምን ወደ ህግ ተቋማት ወይም ወደ ባህላዊ ሽምግልና አይሄድም?" የሚለው ጥያቄ መነሳትና መልስ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ተጨባጭ የሆነ ስጋት በሌለበት ሁኔታ አብዛኛው አርሶ አደር ዱላ ይዞ መሄዱ ወይም መንቀሳቀሱ ጥቅሙ ከምኑ ላይ ነው? አንደኛ - ዱላው አላስፈላጊ ሸክም ነው፡፡ ሁለተኛ - በከተማ አካባቢ በወጉ ለመንቀሳቀስ (ለምሳሌ ወደ ሆስፒታልም ሆነ ወደ ሌላ የመንግስት ተቋም ሲገቡ፣ መኪና ላይ ሲሳፈሩ) ያስቸግራል፡፡ ሶስተኛ - በአጋጣሚ ግጭት እንኳን ቢነሳ በቀላል መሰዳደብ፣ ግፋ ቢልም ለድብድብ በመገባበዝ ሊቋጭ የሚችለው ጠብ፣ ዱላ በመኖሩ ምክንያት ወደ መደባደብ ሊያድግና በአካልና በህይወት ላይ ያልተጠበቀ አደጋ ሊደርስ ይችላል፡፡ አራተኛ - ዱላ የደን ልማት ፀር ነው፤ ከሁለት፣ ከሶስት ወይም ከአራት አመት በኋላ ዛፍ ሊሆን የሚችል "ታዳጊ" ተቆርጦ ነውና ዱላ የሚገኘው፡፡

የዱላ የደን ፀርነት ላይ ላዩን ሲያዩት ቀላል ሊመስል ይችላል፡፡ ትንሽ ሂሳብ ቢጤ በመስራት የችግሩን ክብደት ማሳየት ይቻላል፡፡ አንድ አርሶ አደር ቆርጦ ያዘጋጀው ዱላ፣ በአገልግሎት ላይ እያለ በመሰበር፣ በመሰንጠቅ፣ ወዘተ. በመሳሰለው ምክንያት ዱላነቱ ሊቀር ይችላል፡፡ ወይም አንድ ቦታ ካስቀመጠው በኋላ ረስቶት ሊሄድ ይችላል፡፡ አምና ከፈለገ ህይወት መግቢያ በር ላይ (ከውስጥ በኩል) በመረሳቱ ምክንያት ተከማችቶ ያየሁት እጅግ በጣም ብዙ በትር ለዚህ አብነት ነው፡፡ ዱላው ሊጠፋበት ወይም ሊሰረቅም ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ምናልባትም ዱላው ከእሱ ጋር ያለው የቆይታ ዘመን በተራዘመ ቁጥር "ሊደብረው" ይችላል - አንዳንድ ከተሜዎች የሞባይል ስልካቸው ቀፎ እንደሚደብራቸው አይነት፡፡ እናም አርሶ አደሩ ዱላውን በሌላ ሊቀይር ይችላል፡፡

ይህን ሁሉ ከግምት በማስገባት ለአንድ ዱላ ወይም በትር ግምታዊ የሆነ አማካይ የህይወት ዘመኑ አስር አመት ቢሆን ብለን እናስላ፡፡ በዚህ መላምት መሰረት አንድ አርሶ አደር በአስራ አምስት አመቱ በትር መጠቀም ቢጀምርና እስከ ስድሳ አምስት አመት በህይወት ቢኖር ቢያንስ የተለያዩ አምስት በትሮችን ወይም ዱላዎችን ይጠቀማል፡፡ አምስት ዛፍ ሊሆን የሚችል "ታዳጊ" ተክል ይቆርጣል፤ በሌላ አነጋገር አምስት ዛፍ ይገድላል ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው ሶስት ወንድ ልጆችን ቢወልድ፣ በሱና በልጆቹ የህይወት ዘመን በድምሩ 20 ዛፎችን ይገድላሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ በቆረጡት ልክ ሳይተኩ ብቻ ሳይሆን አንድም ዛፍ ሳይተክሉ የመሆን እድሉ እጅግ የሰፋ ነው፡፡

## ደም መመላለስ

ሌላው ከማህበራዊ ግንኙነትና ከአካባቢ ሰላም አንፃር ያለው ጉዳት ነው፡፡ ሌሎች ጉዳዮች እንደ ተጠበቁ ሆነው ዱላ ይዘው እያለ በአንድ ነገር የተጨቃጨቁና በጠነከረ ሁኔታ እስከ መነቃቀፍ (አንዳንዴ እስከ መዘላለፍም ጭምር) የደረሱ ሰዎች እና ዱላ ሳይዙ ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የወደቁ ሰዎች ወደ ድብድብ የማምራት እድላቸው እኩል አይደለም፡፡ ለጠብና ድብድብ ያላቸው ስነልቦናዊ ዝግጅት በእጅጉ ይለያያል፡፡ በክብደት ማንሳት ስፖርት ሰውነቱን ያፈረጠመ ጎረምሳ፣ ለስፖርቱ ስነምግባር ተገዢ ካልሆነ፣ ለአምባጓሮ የሚቀድመው ላይኖር ይችላል - አካላዊ ዝግጅቱ የስነልቦናዊ ግፊቱን ይጨምረዋልና፡፡

በዱለኝነት ምክንያት የሚደርሰው ሰብአዊ ጥፋት ማለትም ነፍስ ግድያና መዘዙ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ "ደም እመልሳለሁ" በማለት የሚሸፍቱ፣ የደም መላሾችን በቀል በመፍራት የሚሰደዱ፣ በሰፈራቸውም ሆነው ህይወታቸውን በስጋትና በጭንቀት የሚያሳልፉ… ጥቂት አይደሉም፡፡ በተገደለው ሰውዬ የወንጀል ድርጊት ውስጥ በምንም መንገድ ሳይሳተፉ፣ ሰውዬው መገደሉን ጭምር ከአካባቢያቸው ሰው ጋር እኩል ሰምተው ሲያበቁ፣ የገዳዩ የቅርብ ዘመድ ስለሆኑ ብቻ "በደም መላሾች" የበቀል ግድያ ህይወታቸውን የሚያጡ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ህፃናትንና ታዳጊዎችን ጭምር የሚገድሉ "ደም መላሽ" ተብዬዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ከጥቂት አመት በፊት እንደሰማሁት በደሴ ዙሪያ አካባቢ ጠላ ቤት ውስጥ በተፈጠረ ግጭት፣ አንዱ አርሶ አደር ሌላውን በጨለማ መንገድ ላይ ጠብቆ በዱላ ይደበድበዋል፡፡ ለህክምና ደሴ ሆስፒታል ይተኛል፤ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ይሞታል፡፡ መናገር ባለመቻሉ -የሟች ወገኖች - ደብዳቢውን/ገዳዩን ማወቅ አልቻሉም፡፡ የተለያዩ ፍንጮችን በመጠቀም የግላቸውን ማጣራት አካሄዱ፡፡ ከዚያም ገዳይን በተጠርጣሪነት ከሰሱ - ለአገር ሽማግሌዎች፡፡ የአገር ሽማግሌዎች ገዳይን ደጋግመው አነጋገሩ - መግደሉን እንዲያምን እና ወደ እርቅ ድርድር እንዲመጣ፡፡ የገዳይ ቤተሰብ፣ ገዳዩ ድርጊቱን እንዳያምን ወይም እንዲክድ ከፍተኛ ግፊት ስለፈጠሩበት አላደረኩም ብሎ ማለ፡፡

የሟች ወገኖች ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ - ገዳዩን በመግደል ደም ሊመልሱ፡፡ ሳይሳካለቸው ለአንድ አመት አካባቢ ቆዩ፡፡ አንድ ቀን ገዳዩ በሬ ጠምዶ እያረሰ እንዳለ መጡ -ሁለት ወይም ሶስት ሆነው፡፡ ዱላ ሳይሆን የጦር መሳሪያ ("ክላሽ") ይዘው፡፡ ከዚያ ማሳደድ ጀመሩ… ወደ መንደር በመሮጥ፣ ከአንድ ቤት ገብቶ በሩን ከውስጥ ዘጋ፡፡ በበሩ ላይ ጥይቱን አርከፈከፉት፤ እናም ገደሉት፡፡ ከዚያ አንድ፣ ከዚህ አንድ ስለተገደለ ደም ለመመለስ ሲባል የሚፈፀመው የመገዳደል ፋይል ተዘጋ ማለት ግን አይደለም፡፡ በወቅቱ ህፃናት የነበሩት፣ የደም መመለስ አስፈላጊነት እየተተረከላቸው የሚያድጉት የዚህ ሰው ልጆች ለደም መመለስ እንደማይዘጋጁ ምን ዋስትና አለ? ለተጨባጩ እውነት የሚቀርበው፣ ዝግጅት እንደሚያደርጉ፣ የበቀል (ደም የመመለስ) አዙሪኝ ቀለበቱ (vicious circle) ነፍስ ዘርቶ እንደሚቀጥል ነው፡፡

ይበልጥ አሳሳቢው ችግርም ይሄ ነው፤ የደም መመለስ "ባህል" አንድ ከዚያኛው ወገን ስለተገደለ፣ አንድ ከዚህኛው ወገን በመገደሉ የማያቆም መሆኑ ነው፡፡ ደም መመለስ በአዙሪኝ ቀለበት የተበከለ ነው፡፡ የደም መመለስ ድርጊትን በውል ስናየው ደም መመለስ ሳይሆን መመላለስ ነው፡፡ በእዚህ አጉል ልማድ ውስጥ ደግሞ የዱላ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ዱላ የመያዝ ባህል እና ዱለኝነት መመጋገባቸው ብዙም አከራካሪ አይደለም፤ ዱለኝነትና ፍላጎትን በሀይል የማሳካት እብሪትም እንዲሁ፡፡

## ከተሜዎቹስ?

አሁን ደግሞ ወደ እኛ - ወደ ከተሜዎቹ - ፊታችንን እናዙር፡፡

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# እንግዳችን ...

ከገጽ 9 የዞረ

መምህራንና ሠራተኞች እያስተዳደረ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ከአቅም ማነስም ይሁን ሆን ተብሎ አይታወቅም የመልካም አስተዳደር ችግር ይስተዋላል፡፡ ሠራተኛው፣ መምህራንና ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው አመራር አይረኩም፡፡ በተለይ በሠራተኛው በኩል የሚቀርበው አቤቱታ ከቦርድ አልፎ ትምህርት ሚኒስቴር ድረስ እየተሻገረ የዩኒቨርሲቲው ስም በመጥፎ ጐኑ ሲጠራ ይሰማል፡፡

ከመማር ማስተማሩ ጐን የሰራተኛው የሥራ ድርሻ ለዩኒቨርሲቲው እድገት የጀርባ አጥንት ነው፡፡ በዚህ መካከል አመራሩና ሠራተኛው በመካከላቸው ክፍተት ከተፈጠረ የተተለሙት ግቦች ሳይደርስባቸው በመንገድ ላይ ይቀራሉ፡፡ ይህን በመካከላቸው ያለውን ቅራኔ ለመፍታት ቦርዱ ከፍተኛ ሥራ ይጠበቅበታል፡፡ በበርካታ ክፍሎች ሥራዎች በዘፈቀደ እንጅ በፕላንና በእቅድ እየተሰሩ አይደለም፡፡ የከፍተኛ አመራር አካላት ወደ ውስጥ ዘልቀው በመግባት የሠራተኛውን፣ የመምህሩንና የተማሪዎችን ችግር በሰከነ አመራር አይተው እልባት መስጠት አለባቸው እላለሁ፡፡

ንብረት ሲባል እቃ ግ/ቤት ብቻ የተቀመጠው አይደለም፡፡ መኪናው፣ ሕንፃው፣ ዛፎች፣ ወንበሮች ይህ ሁሉ ያረፉበት ቦታ ንብረት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በዓባይ ወንዝ እና በዋናው ግቢ መካከል ያለው ቦታ የዩኒቨርሲቲው ስለነበር አባይ ወንዝ ሞተር አስተክለን ውሃ በመሳብ የመናፈሻ ቦታ ተዘጋጅቶ አትክልቶች ሁሉ  ተተክለው የተመደበው ሠራተኛ በአግባቡ ተንከባክቦ መናፈሻው አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ባልታወቀ ምክንያት ሠራተኛው ተባሮ አትክልቶቹም ተመንጥረው ጠፍተዋል፡፡ ይህ መናፈሻ በነበረው እቅድ ቢቀጥል ተማሪዎች አልባሌ ቦታ ከመሄድ መቆጠብ ይችል ነበር፡፡

ከዘንዘልማ፣ ይባብ እና ማሪታይም ኮሌጆች ውጪ የተሰሩ ሕንፃዎች፣ የቢሮ መገልገያ እቃዎችና የተማሪዎች የምግብ ቤት እቃዎች እንዲገዙ ጥያቄዎች የሚቀርቡት አብዛኛው በእኛ ክፍል ስለነበር በወቅቱ መድረስ እንዲችሉ ክትትል እናደርግ ነበር፡፡ በመሆኑም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እየተጠናቀቁ እና እየደረሱ ፕሮግራሙ እንዲሳካ ይደረግ፡፡ አንድ ጊዜ ትዝ የሚለኝ ነገር እኔ እና አቶ ንጉሴ ካሳሁን በየቦታው እየተቀደዱ የሚወድቁ የማያገለግሉ ወረቀቶችን፣ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡ የፈተና ወረቀቶች እና ሌሎችንም እያሳሰብን አንድ ክፍል ውስጥ ቆልፈን ካስቀመጥን በኋላ በየጊዜው ጨረታ በማውጣት እየተሸጡ ገንዘቡ ለኮሌጁ ገቢ ይደረግ ነበር፡፡ ይህ ስትራቴጂ አንደኛ የአካባቢውን ጽዳት ይጠብቃል፡፡ ሁለተኛ የገቢ ምንጭ ሆነው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ የቴክኒክና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ በነበርኩበት ወቅት ለተሽከርካሪ ስምሪት ክፍል ጠንካራ መካኒኮች ተቀጥረው መኪኖችን መጠገን ይችሉ ነበር፡፡ እስፔር ፓርት እየተገዛ ቀላል የሆኑ ጥገናዎች በራሳችን ባለሙያዎች ይሰሩ ነበር፤ ይህ አሠራር በብዙ መልኩ ወጪ ቆጣቢ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው እያደገ በመሄዱ በርካታ ተሽከርካሪዎች ተገዝተዋል፡፡ እነዚህ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ በየማደያው ሄደው ከሚቀዱ ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ የቤንዚንና የናፍጣ ዲፖ እንዲኖረው ለማድረግ ለማስፈቀድ አዲስ አበባ ደብዳቤ ጽፈን ተስፋ ተሰጥቶን ነበር፡፡ የነዳጅ ማደያው በግቢ ውስጥ መኖር አንደኛ በተፈለገው ጊዜ መቅዳት ያስችላል፣ ለቁጥጥርም አመቺ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በከተማው ውስጥ የነዳጅ እጥረት ሲከሰት በቋት የያዙት ነገር ለክፉ ቀን ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ የጠቅላላ አገልግሎት ክፍል ለብዙ ነገሮች ባይተዋር መስሎ ይታየኛል፡፡ ዳይሬክቶሬቱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙ የመምህራን፣ የሠራተኛና የተማሪዎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በሙሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ስላለው ያገባኛል ብሎ መሥራት ቢጀመር፡፡

የዩኒቨርሲቲው ንብረት የሆነ ሁሉ ለምሳሌ ሕንፃዎች፣ ሕንፃ ያልተሰራባቸው የይዞታ ቦታዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ በቋሚነት የሚያዙ ንብረቶች የዩኒቨርሲቲው ሃብቶች በመሆናቸው ይህ ክፍል አያያዛቸውን በተመለከተ ደንብ እና መመሪያ በማውጣት ጥብቅ አድርጐ ይዞ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ያለበት ይመስለኛል፡፡

ናይል፡- ማመስገን የሚፈልጉት እና ይህ ቀረ የሚሉት ተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት?

አቶ ያረጋል፡- ማመስገን የምፈልገው መላ የዩኒቨርሲቲውን ሕብረተሰብ ነው፡፡ ኃላፊ ሆኘ በሥሬ ከሚሰሩ ሠራተኞች እና አለቆቼ ሆነው ከሚመሩኝ ኃላፊዎች ጋር የነበረኝ ግንኙነት መልካም ስለነበር ሁሉንም አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ አሁን አዲስ የተመደብኩበት ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሥር የሚገኙ ሠራተኞች ወጣቶች፣ ታታሪዎች፣ ፈጣንና አስተዋዮች በመሆናቸው የሚሰሩት ሥራ ፍሬያማ ነበር፡፡ ከእኔም ጋር በጋራ የምንሠራቸው ሥራዎች ስለነበሩ በታላቅነት አክብረውኝ ካለምንም እንከን በምስጋና እንለያይ ስለነበር እነሱንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!

አቶ ያረጋል፡- እኔም አመሰግናለሁ!

# ተመራቂዎች ያገኙትን እውቀትና ...

ከገጽ 5 የዞረ

የእውቀት ፍለጋ ዓመታት በኋላ ለዚህ የምረቃ በዓል በመድረሳቸው የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ የተመራቂ ወላጆችም የልጆቻቸውን የመጀመሪያ የህይወት ፍሬ ለማየት በመብቃታቸው ታላቅ ኩራት ሊሠማቸው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር አለማየሁ አክለውም በሀገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ የህብረሰቡን የጤና ሽፋን ከፍ ለማድረግ ገና ብዙ መሠራት እንደሚገባ የሚያመላክቱ በርካታ ነገሮች እንዳሉ ጠቁመው ዩኒቨርሲቲው ይህን ችግር ተገንዝቦ ለሶስተኛ ጊዜ የህክምና ዶክተሮችን ለማስመረቅ መብቃቱ የአመራሮች ቁርጠኝነትን የሚያሳይ በመሆኑ ወደፊትም ከዚህ በበለጠ እንዲሠራ አስገንዝበዋል፡፡ የህክምና ትምህርት ክቡር የሆነውን የሠው ህይወትን ለመርዳት ከፍተኛ ኃላፊነት በመሸከም በአግባቡ ማገልገል የመንፈስ እርካታ ስለሚሠጥ ተመራቂዎች በትምህርት ያገኙትን እውቀትና ክህሎት በአግባቡ በተግባር ላይ በማዋል ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

ተመራቂዎች በሥራው ዓለም ሲሰማሩ የህክምና ህጎችን አክብረውና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ይሠሩ ዘንድ የሚያዘውን ቃለ-መሃላ በህክምና ኮሌጁ ኃላፊ በዶ/ር ሀብታሙ ባየህ አማካኝነት ገብተዋል፡፡

ከወንድ እጩ ተመራቂዎች መካከል ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገበው ዶ/ር ፍስሐ ገበየሁ "ያስተማረኝ አባቴ ከጎኔ ባይሆንም እንድሆንለት የሚፈልገውን ሆኜ ፍላጎቱን ስላሟላሁለት እጅግ ደስ ብሎኛል፤ በገነት ነፍሱ ትደሰትልኝ" ብሏል፡፡ ከሴት እጩ ተመራቂዎች መካከል ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገበችው ዶ/ር አመለወርቅ ሰለሞን በበኩሏ በሀገራችን ያሉ ሆስፒታሎች የሚፈለገውን የህክምና መሣሪያ አሚልተው ባይገኙም ባለውና ባካበትነው እውቀት የቻልነውን ሁሉ በማድረግ ጠንክረን እንሠራለን ስትል ሀሳቧን ገልፃለች፡፡ በምረቃው ስነ-ስርዓት ላይ በዩኒቨርሲቲው ባሕል ማዕከል ውዝዋዜና የእንኳን ደስ አላችሁ መዝሙር ያቀረበ ሲሆን የፖሊስ ባንድ ማርሽ ትርኢት ለበአሉ ድምቀት ሰጥቶታል፡፡

# የቴክኖሎጂ ተቋም በኮንስትራክሽን ...

ከገጽ 5 የዞረ

ጥራት በማስጠበቅ እንዲሁም ከአላስፈላጊ ብልፅግና ራሳቸውን በማራቅ ለሙያቸው ክብር መስጠት እንዳለባቸው ምልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በበኩላቸው አንዳንድ ሀገሮች መሀንዲሶቻቸው በትምህርት ያገኙትን ንድፈ ኃሳብ በተግባር በመተርጐም በዘርፉ ያላቸውን የሰው ኃይል ለአለም ገበያ በማቅረብ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ በመቻላቸው ድህነትን አሸንፈው ከበለፀጉ ሀገራት ተርታ መሰለፍ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል፡፡ ተመራቂዎችም በሥራ ዘመናቸው በንባብና ምርምር እውቀታችሁን በማበልፀግ መንግስትና ሕዝብ የጣለባቸውን አደራ በመወጣት የኮንስትራክሽን ዘርፉን ወደላቀ ደረጃ ማሸጋገር እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የተመራቂ ተማሪዎች ተወካይ ኢንጅነር አለማየሁ ያዛቸው እንደተናገረው በእውቀትና በክህሎት በልጽገን አገራችንን በተማርነው የሙያ መስክ እንድናገለግል እገዛ ላደረጉልን ተቋማት ምስጋና እናቀርባለን ብሏል፡፡

# ማዕከሉ ለሴት ሥራ ፈላጊ

ከገጽ 4 የዞረ

ቢታወቅም ሴቶችን ከማበረታታትና አቅማቸውን በኢኮኖሚም ሆነ በማህበራዊ እሴቶች ከመገንባት አኳያ ታስቦ እድሉ እንደተሰጣቸው አስገንዝበው ዩኒቨርሲቲው የዕለት ከእለት እንቅስቃሴአቸውን በመከታተል የሚሰጠውን ውል እንደአስፈላጊነቱ የሚቀያይር መሆኑን አሳስበዋል፡፡

የኢንተርፕርነርሽፕ ልማትና ማበልፀጊያ ማዕከል ዳይሬክተር ወ/ሮ አለምፍሬ ደረሰ የስልጠናው ዋና ዓላማ ለሰልጣኞች የስኬታማ የንግድ ሥራ ፈጣሪዎችን ባህሪያት ለማስረፅ ግላዊ ኃላፊነት የተሞላበት ተግባራዊ እርምጃ ለስኬት አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ እና ስኬታማ የንግድ ሥራ ፈጠራ አማራጮችን በምሳሌያዊ አስተምህሮ ለማመላከት ነው ብለዋል፡፡ ወ/ሮ አለምፍሬ አክለው ስልጠናው የተዘጋጀው ሰልጣኞች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ለመፍጠር እንደመሆኑ መጠን በንግድ ሥራው ዓለም መበልፀግ እንዳለ ሁሉ ውድቀትም ስላለ ለወደፊት የሚገጥማቸውን ማንኛውም ችግር ለመወጣት እንዲችሉና ወደ ሌላ ወገን ሳያሳብቡ ወደራሳቸው እንዲያመጡት የምክክር መድረኩ የጐላ ፋይዳ እንዳለው አስገንዝበዋል፡፡

በስልጠናዉ ወቅት ስለ ንግድ ሥራ ፈጠራ የሚያወሩ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተው ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በነፃነት በመግለፅና በውስጣቸው ያለውን የንግድ ሥራ ዝንባሌ በማንፀባረቅ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

# ተቋሙ የአውሮፓ ኮሚሽን ...

ከገጽ 5 የዞረ

ዩኒቨርሲቲ /University of Leuven/ እንዲሁም ከአንድ አለም አቀፍ የመሬት መረጃ አመዘጋገብና አያያዝ አማካሪ ጋር በመሆን ባቀረበው ሃሳብ ይህንን የገንዘብ ድጋፍ አግኝቷል፡፡

የአውሮፓ ኮሚሽን ‹ሆርዞን 2020› / Horizon 2020/ በተባለው የምርምርና ፈጠራ (Research and Innovation) ኘሮግራሙ በኩል በጅኦስፓሻል / Geospatial/ ቴክኖሎጅ ችግር ፈች የምርምር ሃሳቦችን በገንዘብ ለማገዝ ከ2014 እስከ 2020 (እ.ኤ.አ) ባሉት ሰባት ዓመታት ወደ 80 ቢሊዮን ዩሮ የሚጠጋ ገንዘብ በጅቷል፡፡

የ'Its4land' ኘሮጀክት ዋና አላማ መሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን በሰው አልባ ድሮን (Unmanned Aerial Vehicle (UAV) መሰብሰብ ነው፡፡ በሰው አልባ ድሮን የሚሰበሰበው መረጃ ካዳስተራል ዳታን በተጠቀሱት የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ማሻሻያ ለማድረግና ያለውን የቀድሞው አሰራር በማሻሻል የመሬትን ተጠቃሚነትንና ባለቤትነት በማረጋገጥ በቀጠናው የተቀናጀ የማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያፋጥናል፡፡ ይህ ፕሮጀክት በዋናነት በምስራቅ አፍሪካ በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በሩዋንዳ እንዲሁም በሌሎች የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይህ ኘሮጀክት ተግባራዊ ሲሆን በተለይ የኢትዮጵያ መንግስት ለመሬት መረጃ አመዘጋገብና አያያዝ (Cadastre) እየሰጠው ካለው ትኩረት አንፃር እንደግብዓት ያግዛል ተብሏል፡፡

# Revisiting (Good) Governance ...

continued from page 6

the degree to which a client country would be having a liberal democratic state in a pluralist society.

The third meaning of Governance is inferred from the explanatory ideal, since governance highlights the importance of rule of law, human rights, participatory development and democratization. As against the managerial position of governance, the ethical-normative dimension connects Governance to some of the older issues in the discipline of Political Science particularly to that of Political Theory. As it is well known, State, as the classical Greeks Philosophers said, "stands for good life". Viewed from this ancient golden sentence, it is not enough that public administration is running on sound managerial principles. Because, the equity and legitimacy aspects are as important, or perhaps more important, than good management. And, the governing process should provide opportunities for the people to actively participate in decision-making and the fruits of government must be universally shared and not captured by an influential minority. What is important to remind here is that people's perception about how the governing process is going on serves as the barometer (weatherglass) for the equity and legitimacy aspects of governance. Thus, empowering citizens is considered as a necessary precondition of good governance.

In relation to the first and third conceptualizations of governance, it has been commented that the concept of Good Governance is a withdrawal from the excessively formalistic character of conventional public administration. In contemporary complex world of governing, it is remarkably stressed that government alone is not capable of coping with the innumerable problems confronting the society or our community today: climate change, shortage of land, population pressure and food insecurity, pervasiveness of criminal acts, and above all natural resources depletion and loss of bio-diversity. Of paramount importance, therefore, is maximizing all available chances of networking with all available political, socio-cultural, economical, religious institutions, groups or individuals which have the potential to enhance the capacity of governance in the larger society as a whole. It is also noted that this will facilitate the development of social, financial and human capital through the agreed involvement of social groups so as to solve the prevailing community or societal problems. Again, it is believed, to the extent that governance would be bring about transparency, openness, rules of law and human rights observance, the tradition of collective problem-solving setting will facilitate consolidation of democracy.

Merely, the second aspect of Governance which links it with aid giving conditionality has been judgmentally reviewed by many critics. For instance, one kind of argument has been that the World Bank is seeking to politicize the otherwise technical issue of financial aid to the developing countries. There are also other arguments which declare that Good Governance is a one-dimensional notion, as there are diverse ways of governing in countries with multi-cultural contexts. Put simply, Good Governance, as the critics point out, seems the revival of "one right way" principle of classical administrative theory to do something like that of the scientific management school of Fredrick Winslow Tylor which is resurrected naively to the contemporary world situation that demands more cooperation and flexibility in governance than rigidity of any kind.

Surprisingly, if the practice of Good Governance is accused of rehashing one-best principle of doing things like that of the scientific management school. This means, it is at odds with current public administration approaches such as Management by Objectives (MBOs), Business Process Improvement initiatives (BPIIs), Business Process Reengineering (BPR), and other tools similar to them. Because, these reform approaches promote individual responsibility and seek to push decision making through all levels of the organization. So, how is it going to be reconciled? Further research is expected from BDU's scientific community.

However, the strongest criticism of governance is forwarded by Haque (2000) especially on its principle of accountability. To quote Hague, "It is essential to understand that the accountability of public governance for market based economic performance does not guarantee its accountability for representation and equality, and its accountability for higher profit does not connote its accountability for social welfare and justice."

Through a gradual process governments in democratic societies have increasingly become accountable to diverse groups and classes of citizens that are entitled to social services such as education, housing, health and social security. It is also publicized that the people-centered convention of accountability have been evolved by the advent of inclusive civil society organizations in general and by organized working class in particular; which results in an increase in the entitlements or rights of common citizens. Yet, under this new paradigm of good governance, it is argued that citizens have been redefined as customers or clients; which is a commercial view of citizenship. This kind of citizenship, in its turn, is accused of reducing the social rights that are related with collective citizenship to narrow commercial privileges of individual customers who are governed by exchange relationships.

With regard to the reductionist interpretation, Hague argues, " Public governance is accountable for the effective delivery of it services to customers ***who can pay*** while it may remain indifferent towards low-income citizens who are not in a position to use such services due to their financial incapacity."Accountability, under this consumerist mode of governance is dedicated to those private and wealthy customers rather than to the collective public, that means, the poor majority**;** and in consequence, the economically disadvantaged citizens, who often depend on the state for basic services, do not meet the criteria of being a customer for not being able to afford user charges. As the critics point out, this customer view tends to diminish citizens' rights vis-à-vis the state, and excludes common citizens from the Calculation of Public Accountability (CPA). Accordingly, therefore, it has been alleged that Public Governance today has become more accountable and responsive, not to the larger poor sections of society, but to the wealthy business community. In other words, the missions of Good Governance are hijacked by the affluent business community. Its commitment to social justice, equity, legitimacy, empowerment, and, above all, to social welfare mentioned earlier, appears to be ignored.

All in all, governance can be seen from the view of those three grand pillars. Primarily, it refers to establishing links with all formal, non-formal, and informal institutions, groups or individuals. In other words, to solve societal or institutional problems, a Networks of Multiple Agencies (NMA) are needed. From this connotation of Governance, I sense that we can think of problems in the university which can be solved by establishing a Network of Multiple Agencies (NMA). In my view, this conceptualization of governance is under-exploited. Secondly, it refers to applying principles of accountability, rule of law, transparency, responsiveness, participation, inclusiveness and equity, efficiency and effectiveness, and consensus building. Though not all of them, some of the principles of governance in this connotation are also pronounced by our daily practices in the university. Yet, assessing the university's human resources' perceptions towards those principles and about how the university's governing process is going on particularly by using the governance barometer (weatherglass) is a missed element. This also demands further research from BDU's scientific community. The third connotation of governance is associated with "*Who Gets What and Why"*share of resources. In the context of the university, this can be seen in terms of budget allocation among faculties, institutes, researchers, or other incentive mechanisms designed to motivate employees. Particularly, in each college/faculty/institute/research center, the practices of research budget allocation needs further scrutiny. The typical example, from observation, I learnt that faculty research and community services coordinators and deans have the right to conduct research 'if they have the time'. And, they submitted proposals for university funding. This is, still, fine. The problem I observed is that, they also participated in the decision making procedure of research budget allocation for submitted proposals (sometimes, there is possibility of approving budget for own proposal; of course along with committee). Here, can we conclude that they will decide rationally without the influence of their rudimentary instincts – emotions and desires? Still, can we conclude that they will be free from the negative effects of group dynamics in the decision making circle? This is because, there are possibilities of team, personal, leadership, and environmental factors that can affect the act of working together well of the group (committee).This seems also unnoticed thematic area which needs further research.

Thus, from all these syntheses of literature sources and personal reflections, I feel that there is a need to reexamine the practices of Good Governance based on the three pillars stated above. There appears also the need to conduct further research at regional/national level to develop an alternative model dedicated to ensuring transparency and accountability to the larger poor sections of the society. In this regard, the scientific community of the university has much more miles to go to supply research findings that will have potential impact on the policy makers as well as implementers. A governance model which is deeply rooted in the indigenous Ethiopian community must grow up to transform the Ethiopian public administration into a reality than a virtual people's administration. Instead of the good governance model suggested by World Bank and OECD countries which is; undeniably, top down in its approach, there is a need to formulate Grass Root Governance Model (GRGM) that will be accountable and responsible to the common man, the needy and the down-trodden sections of society. A governance model that integrates the interests of citizens of developing countries is urgently needed! It is high time we dealt with it.

# ዱላና ዱለኝነት ...

ከገጽ 11 የዞረ

አንዳንድ የኔ ቢጤ ከተሜዎች ባዶ እጃቸውን ስለሚንቀሳቀሱ ዱላ ከመያዝ ባህላዊ ተፅዕኖ ራሳቸውን ነፃ አድርገው ያስቡ ይሆናል፡፡ ጥቂት የማይባሉ ከተሜዎች፣ ባንድ ወይ በሌላ መንገድ ዱላ ከመያዝ ከሚመነጨው፣ ከትልቁ ተፅእኖ ማለትም “ከዱለኝነት ስነ ልቦናዊ ሰለባነት ያመለጡ ናቸው” ብሎ መደምደም ሊያስቸግር ይችላል፤ አብዛኛው ሰው የገጠሩ ማህበረሰብ ውጤት ከመሆኑም በላይ በገጠሩና በከተማው ባህል መካከል መወራረስ ስላለ፡፡ ለዚህ እውነታ በርካታ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

ባለፈው አመት በሳውዲ አረቢያ ሪያድ ከተማ ውስጥ በሚገኘውና “መንፉሃ” ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ ያሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የፈፀሙት ድርጊት ለዚህ አንድ ማሳያ ነው፡፡ በማህበራዊ ድረ ገፆች የተሰራጨው ዜና እንዳመለከተው ኢትዮጵያውያኑ በጎሳ ቡድን መስርተው፣ በጠራራ ፀሀይ ሳይቀር እየተገዳደሉ ነበር፡፡ ዜናውን ሳነብ በሁለት ነገር ልቤ ክልቡ አዘነ፤ አንድ ይህን ያህል በሚያስጠላ የጠላትነት ጎራ በመከፋፈል መገዳደል ውስጥ በመግባታቸው፤ ሁለት - ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ እንጀራ ፍለጋ በሄዱበት የባእድ አገር በመሆኑ፡፡

ይህ የሳውዲው ክስተት ከአራት አመት በፊት በህንድ አገር የአንድ ወረዳ ከተማ በሆነችው ቪሻካፓትናም ውስጥ ትምህርት ላይ በነበርኩበት ወቅት በአሜሪካ አገር ስላሉ ኢትዮጵያውያን ከአንድ ህንዳዊ የሰማሁትን “ታሪክ” አስታወሰኝ፡፡ አብዛኛዎቹ የተማሩ ህንዶች አንድን ሰው ህንዳዊ አለመሆኑን ካወቁ፣ “ከየት አገር ነው የመጣኸው?” ብሎ ለመጠየቅና ለመተዋወቅ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ወደ አንድራ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ሳቀና ያገኘኝ ህንዳዊም እንዲሁ በድንገት ተዋወቀኝ፤ ወይም እንድትዋወቀው አደረገኝ ብል ይሻላል፡፡ ከየት እንደ መጣሁ፣ ለምን እንደ መጣሁ፣ ትዳርና ልጅ ያለኝ ስለመሆኑ፣ ወዘተ. አከታትሎ ጠየቀኝ፡፡ ህንዶች እንደ'ዚያ ናቸው፡፡ ሲወስዱ ሁሉንም መረጃ ነው የሚቀበሉ፡፡ ከዚያም ስለራሱ ነገረኝ - ምን፣ የት እንደሚሰራ፣ ስለትዳሩ ሁኔታ፣ ወዘተ. ህንዶች መረጃ ሲሰጡም እንደዚያው ናቸው - ሁሉንም መረጃ ነው ያለ ስስት የሚለቁት፡፡

ከትውውቁ ቀጥሎ ያቀረበልኝ ጥያቄ፣ “ኢትዮጵያውያን ጠብ አጫሪና ተደባዳቢዎች ናቸው አይደል?” የሚል ነው፡፡

“እንዴት?”

ድንገት የተዋወቀኝ ሰው ያልጠበኩትን ጥያቄ ድንገት ሲያቀርብልኝ ከዚህ ሌላ ልናገረው የምችለው ቃል አልነበረኝም፡፡ ሰውዬው ጥያቄ ቢያቀርብም፣ ነገሩ ጥያቄ አይደለም - ቢያንስ በተዛዋሪ አቋም ወይም እምነት ተደርጎ የተወሰደን ሀሳብ ያንፀባርቃልና፡፡ ስለዚህም ማብራሪያ እንዲሰጠኝ ጠየኩት፡፡

ቪሻካፓትናም ውስጥ እንደ ተዋወቅኳቸው አብዛኛዎቹ ህንዶች ኢትዮጵያን በስም እንኳ “በመልክ” (አፍሪካ ውስጥ የት እንዳለች) አያውቃትም፡፡ ስለኢትዮጵያውያን ባህሪ ያጫወተው አሜሪካ አገር የሚኖር ወንድሙ ነው፡፡ ወንድሙ እንደ ነገረው አሜሪካን አገር የሚኖሩ ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያን በጩቤ እየተወጋጉ ይገዳደላሉ፡፡ ኢትዮጵያውያኑ እንጀራ ፍለጋ በሄዱበት አገር ተስማምተው መኖር አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን መገዳደላቸው፣ መገዳደላቸው ብቻ ሳይሆን የሚገዳደሉበት መንገድ በጩቤ በመወጋጋት ጭምር መሆኑ ይህን ህንዳዊው እጅግ አስገርሞታል፡፡ ስለኢትዮጵያ የሚያውቀው ትልቁ ነገርም ይሄው ነው፤ ለዚህም ነው እንደ ተዋወቅን ይህን ጉዳይ የመጀመሪያ ጥያቄው ማድረጉ፡፡

አሜሪካ የሚኖሩ ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያን፣ “የዲቪ” እጣ “ቀንቷቸው” ከኢትዮጵያ አዲስ ለሚሄዱ ወገኖቻቸው “መጡብን” በሚል ስሜት ጥሩ ፊት እንደማያሳዩና ጥቂቶችም ህንዳዊው በጠቀሰው መንገድ እንደሚገዳደሉ ከዚህ በፊት አንድ የአማርኛ መፅሄት ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በሄዱበት አገር “የሚከተሉት” የዱለኝነት ባህሪ በተለይም የባህሪው የትግበራ መንገድ ምን ያህል ዋጋ እያስከፈላቸው ለመሆኑ ደሴ የማውቀው የወጣቱ ሙሀመድ ታሪክ እዚህ ላይ ጥሩ አብነት ነው፡፡ ሙሀመድ በሾፌርነት ሙያ ወደ ሳውዲ አረቢያ የሄደበት የስራ ኮንትራት ውል በመቋረጡ ወደ ሀገሩ ተመልሷል፡፡ የዛሬ ሁለት አመት ገደማ እዚህ ባህር ዳር በተገናኘንበት ወቅት እንደ ነገረኝ ኮንትራቱ የተሰረዘበት ከእኛዎቹ አገር ልጆች (ኢትዮጵያውያን) ጀብደኝነት ወይም ዱለኝነት ወይም ህንዳዊው እንዳለው “ጠብ አጫሪነትና ተደባዳቢነት” ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነው፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ የሾፌርነት አገልግሎቱን የሚሰጠው ሪያድ ከተማ ውስጥ ለሚገኝ አንድ ቤተሰብ ነው፡፡ ልጆችን ት/ቤት መውሰድና መመለስ፣ ሚስትዬዋን ጨምሮ ሌሎች የቤተሰቡ አባላትን ወደ ገበያና መዝናኛ ቦታ መወስድና መመለስ፣ ወዘተ. ዋና ስራው ነበር፡፡ ስራው አድካሚ ካለመሆኑም በላይ ደመወዙ ደኅስ ያለ ነበር፡፡ ከቤተሰቡ ጋር ተግባብቶ እየሰራም ነበር ያለው፡፡

በመሀሉ አንድ ነገር ይከሰታል - በአንድ ኢትዮጵያዊ የተፈፀመ የግድያ ወንጀል፡፡ ሙሀመድ እንደ ነገረኝ አምስት የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ቁጭ ብለው እየተጫወቱ እንዳሉ፣ አንዱ (ቀደም ሲል በነበረ አለመግባባት ቂም ይዞባቸው የነበረ) ጩቤ ያወጣና አራቱን ወይም ሶስቱን፣ በእሱ አነጋገር “ጨቅ፣ ጨቅ” ያደርጋቸዋል፡፡ የሞተም ሞተ፣ የቆሰለም ቆሰለ፡፡ ከዚያ ክስተቱን መገናኛ ብዙኃን አናፈሱት (ለዚህማ ማን ብሏቸው!)፡፡ ዜናው ከሁሉም ጆሮ ደረሰ፡፡

በዚህ ወቅት የሙሀመድ አሰሪ ውጭ አገር ነበር፡፡ ሚስቱ ስልክ በመደወል የግድያውን የወንጀል ዜና ከነገረችው በኋላ የሙሀመድን የሹፌርነት ኮንትራት እንዲቋረጥ እንዲያደርግ ታሳስበዋለች፡፡ ባልዬው የሙሀመድን መልካም ፀባይ (ሰው አክባሪነት፣ ጭምትነትና ትሁትነት) እንዲሁም ታታሪነት በማውሳት፣ እሱን ማባረር እንደማይገባ ደጋግሞ ያስረዳታል፡፡ ሴትዬዋ ግን “አንድ ቀን ሊገድለን ይችላል” በማለት በአቋሟ ፀናችን፡፡ ሙሀመድ እንደ ነገረኝ ለባሏ የሰጠችው ዋና ምክንያት “ሀበሻ ወፊፌ ነው” የሚል ነው፡፡ “ሙሀመድ አሁን ጭምትና ጥሩ ፀባይ ያለው ቢሆንም ልክ እንደዛ ኢትዮጵያዊ አንድ ቀን ድንገት ‘ጨቅ፣ ጨቅ’ ያደርገናል” ማለቷ ነው፡፡

አምና ህዳር ወር መጨረሻ አካባቢ ለአንድ ኮንፈረንስ አዲስ አበባ በቆየሁባቸው በአንዱ ቀን፣ በጴጥሮስ አደባባይ በኩል ወደ መርካቶ የሚወስደው መንገድ፣ በባቡር መንገዱ ግንባታ ምክንያት ጎዳናው ለተሽከርካሪ በመዘጋቱ የግራውን መስመር ይዤ በእግሬ ወደ መርካቶ እያመራሁ፣ አትክልት ተራ ልደርስ አስር እርምጃዎች አካባቢ ነው የቀረኝ፡፡ በስተቀኝ በኩል ኹካታ ቢጤ ተነሳ፡፡ አይኖቼን አሻግሬ ላኩ፡፡ የመንገደኛው ሁሉ ቀልብ ወደዚያው ሮጠ፡፡ በመካከላቸው እስከ አፍ ጢሙ የተሞላ የቆሻሻ ገንዳ ስላለና ዙሪያውን ያለው ውክቢያም ስለበዛ፣ በስተማዶ ያለነው መንገደኞች ለወዲያው ምን እንደ ተፈጠረ ለማወቅ አልቻልንም፡፡ ብዙም ሳይቆይ ነገሩ ግልፅ እየሆነ መጣ፡፡ በግምት አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ወጣቶች ናቸው እየተጫጩሁ ያሉት፡፡ ጥቂቶቹ በሁለት እጃቸው፣ ቀሪዎቹ በአንድ እጃቸው ከመዳፎቻቸው የተረፈ፣ ጣቶቻቸውን የፈለቀቀ ድንጋይ ይዘዋል፤ በያዙት ያበጠ ድንጋይም አንድን ወጣት በማስፈራራት ላይ ናቸው፡፡ ለአንድ ወጣት ይህ ሁሉ ያበጠ ድንጋይ መነጣጠሩ እያስገረመን እንዳለ፤ ወጣቱ፣ ከመቅፀበት ወደ ማዘጋጃ አቅጣጫ ፈትለክ ብሎ መሮጥ ያዘ፡፡ ባላንጣዎቹ ብዙም አልተከተሉትም፤ ሞክር አድርገው ተውት፡፡ ልክ ሩጫውን እንደ ጀመረ አንድ ነገር ግልፅ ሆኖ ታየን - ማዶ ላለነው ሰዎች፡፡ ወጣቱ ጩቤ ይዞ ነው በመሮጥ ላይ ያለው፡፡ የጩቤው ስፋትና ከላዩ ላይ ይፈነጥቅ የነበረው ነፀብራቅ አሁን ድረስ አይኔ ላይ አለ፡፡

እዚህ ላይ የገጠሩ ዱላ፤ ተፈጥሮውን ከእንጨት ወደ ብረት፣ አያያዙን ከእጅ ወደ ጉያ ስለቀየረ በገጠር ያለው የዱለኝነትና ፍላጎትን በሀይል የማሳካት ባህል በከተሜዎቹ ልቦና ውስጥ የለም ሊባል አይችልም፡፡ ይልቁንም “ጥቂት” የማንባል ከተሜዎች የዱለኝነት ወይም ፍላጎትን በሀይል የማሳካት ሰላባዎች ለመሆናችን ብዙ-ብዙ ማሳያዎች አሉና ምርምር የሚሻው ጉዳይ አይደለም፡፡ ሊያጠያይቅ የሚችለው ይህ ባህሪ፣ ዱላ ከመያዝና ከመጠቀም ባህል ጋር ያለው ዝምድና ይመስለኛል፡፡ እኔ በበኩሌ ሁለቱ ጉዳዮች “የምክንያትና ውጤት ትስስር አላቸው” ባይ ነኝ፡፡

## ከችግሩ እንዴት እንውጣ?

ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን በማንሳት መጣጥፌን ልቋጨው፡፡ አንደኛ፡- የተለየ ችግር በሌለበት ሁኔታ ዱላ ይዞ መንቀሳቀስ እያስከተለ ያለውን ችግር በጥልቀትና ዘርዘር ባለ መንገድ ማጥናት፡፡ ሁለተኛ፡- አርሶ አደሮች የተለየ ችግር ከሌለ በስተቀር፣ ዱላ ይዞ የመንቀሳቀስ ልማዳቸውን እንዲቀንሱ፣ ቀስ በቀስም እንዲተዉ ለማድረግ የሚያስችል በትምህርት ላይ የተመሰረተ ስርአት መዘርጋት፡፡

ሁሉም ነገር በማስተማር የመጀመሩን ጉዳይ እዚህ ላይ ደመቅ አድርጌ ላሰምርበት እፈልጋለሁ፡፡ የወረታ ከተማ ፖሊስ እንዳደረገው በግዴታ፣ ዱላ ነጠቃ ውስጥ በመግባት መሆን የለበትም፡፡ በግዴታ የሚጀመሩ የለውጥም ሆኑ የልማት ስራዎች፣ የለውጡ አካል መሆን የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ሌላ ማሊያ በማልበስ በተቃራኒው ሜዳ እንዲሰለፉ ያደርጋሉ፡፡ ሰዎች የለውጥ ጥሪውን በጥርጣሬ አይን ስለሚያዩት ወይ ማሊያቸውን ቀይረው ለውጡን ይታገሉታል፤ እናም ነባሩን ሀሳባቸውን ወይም አቋማቸውን ይበልጥ አጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ወይም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ከለውጡ እንቅስቃሴ ጋር ከተጓዙ በኋላ “ወራጅ አለ” በማለት መንገድ ላይ ይቀራሉ፡፡

ሁለቱም ህብረተሰቡ የሚውስዳቸው ምርጫዎች ለውጥን የሚያደናቅፉ ናቸው፡፡ ለውጡ እንዲደናቀፍ በር ከፋቹና መንገድ ጠራጊው ግን ባብዛኛው እኛ “ተምረናል” የምንለው ነን፡፡ ስለሆነም በትክክለኛ ጥናትና ሳይሰለቹ በማስተማር ላይ የተመሰረተ መርኃ ግብር ቢቀረፅ መልካም ነው - የዱላና ዱለኝነት “ባህልን” በመግራትና ተያያዥ ችግሮችን በመፍታት የማህበረሰቡን በተለይም የአርሶ አድሩን ህይወት ትርጉም ባለው መንገድ ለመቀየር እንዲቻል፡፡

(አብዛኛዎቹን የፉከራ/ቀረርቶ ግጥሞች በመስጠት ለተባበሩኝ ለስራ ባልደረቦቼ ለሐሰን ኡስማንና ለቢሰጥ አያሌው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡)

**ሰላም ለሁላችን!**

To follow the latest news about BDU, check out our website፡-
**http://www.bduinfo63@bdu.edu.et**
**or**
**http://www.bdu.edu.et**
facebook page:-
**www.facebook.com/bduethiopia**

# ጉድ ሰራችኝ ...

ከገጽ 10 የዞረ

አቢ፡- እና ይህ ሁሉ ሆኖ እምቢ አለች?

ቢኒያም፡- አዎ ጨረሶ አትፈልግም የሚገርመኝ ልበሙሉነቷ የምታወራቸው ነገሮች አሳማኝ መሆናቸው ነው፡፡ ካሌብ ግን እጅግ እየጠናበት ሄዷል፤ ምክንያታዊ መሆን እንኳን አልቻለም፡፡

አቢ፡- እንዴ! ካሌብ ነው እየተወራጨ የሚመጣው ?

ቢኒያም፡- የት ነው ያለው?

አቢ፡- ያውልህ የሆነ ነገርማ ሆኗል፡፡

ካሌብ፡- ወይኔ ወይኔ ወንዱ፡፡ እኔን እምቢ!! እንዴት አንዲት እንስት? ልቀበለው የማልችለው እንደ "ሚራክል" የማየው ጉድ ነው፡፡

ቢኒያም፡- ካሌብ ምን ነካህ? አፍህ ደግሞ ምንድን ነው የምትሸተው? / ጠጋ ብሎ ያሸተዋል / እህ … እንዴት በሩን አለፍክ መጠጥ …?

ካሌብ፡- ምን አዲስ ነገር አለ በቃ በደንብ ለማሰብ ስል ያደረኩት ነው፡፡ አቢ አለህ እንዴ ምነው ድምፅህ ጠፋ?

አቢ፡- አስገርመኸኝ እኮ ነው፡፡ እንደዚህ ትሆናለህ ብዬ ጠብቄ አላውቅም፡፡

ካሌብ፡- እንዴት ምን ይገርማል? (የስቅታ ድምፅ ያሰማል፡፡) ይልቅ ቢኒ ወዳጄ አንዴ ወደ ተፋጠጥ እንሂድ፡፡

ቢኒያም፡- ለምን? ምን እናደርጋለን ?

ካሌብ፡- በቃ ዛሬ መፋጠጥ እፈልጋለሁ አግኝቻት ቁርጡን ማወቅ፡፡

ቢኒያም፡- እንደዚህ ሆነህ?

ካሌብ፡- ምን ሆንኩኝ? ምን ታካብዳለህ? ይልቅ የጓደኝነትህን አንዴ ተባበረኝ፡፡

ቢኒያም፡- ግን መጠንቀቅ አለብን፡፡ "risk" አለው

ካሌብ፡- ምንም ችግር የለም እኔን አየኸኝ አይደል፡፡ በደንብ ነው የጠጣሁት ግን ወልገድ እንኳን አላልኩም ንግግሬም የተኮላተፈ አይደለም፡፡ ነው እንዴ?

ቢኒያም፡- አይደለም ሌላ ችግር እንዳይፈጠር ማለቴ ነው፡፡

ካሌብ፡- ግድ የለም እንሂድ

ቢኒያም ፡- እሺ

---------------//--------------

ማርታ ፡- አቤት ለምን ፈለግከኝ;

ካሌብ፡- እያወቅሽው!! በፍቅርሽ ተሸንፌያለሁ መልስሽን ስጪኝ፡፡

ማርታ፡- መልሴን እኮ አሳውቄሃለሁ፤ ፍቅር እያሻኝም አልፈልግም፡፡

ካሌብ፡- እርጅኝ! (ዓይኑን እያስለመለመ እጆቿን በሁለት እጆቹ ውስጥ ቀብሮ)

ማርታ፡- እንዴት አድርጌ? ገንዘብ፣ ቁስ ወይም ሌላ ነገር እኮ አይደለም ህይወት ነው፡፡ የማልፈልገው ነገር ውስጥ እየገባሁ ልረዳህ አልችልም (እጇን ለማስለቀቅ ትታገላለች)፡፡

ካሌብ፡- "at least" ፍቅሬን እንዲስታምም አብረሽኝ ሁኚ፡፡

ማርታ፡- የማይሆን ጨዋታ ነው ይልቅ በጊዜ ከኔ ብትርቅ ይሻልሃል፡፡

ካሌብ፡- "የማይሆነው ጨዋታ ይህ ነው" ካንቺ መራቅ ደግሞ የማይሞከር፡፡

ማርታ፡- እንግዲህ ከዚህ በላይ የማዋራህ የለኝም፤ የምንግባባም አይመስለኝም (ሙሉ በሙሉ እጇን ከእጁ አስለቅቃ)፡፡

ካሌብ፡- ለመሆኑ አንቺ ማን ስለሆንሽ ነው የምትንቀባረሪብኝ እኔ እኮ ካሌብ ወንዱ ነኝ፡፡

ማርታ፡- እኔ ማርታ ነኝ፡፡ ያንተን ፍቅር ያለተቀበልኩ ሴት ምን ታደርገኛለህ?

ካሌብ፡- እገልሻለሁ፡፡ እንደውም አሁኑኑ እጀምርለሁ

ማርታ፡- ወንድነት ላንተ መግደል ብቻ ነው አይደል? ራስን መግዛትና ማሸነፍ፣ ራስህን መቆጣጠር ግን አትችልም፡፡ አሳዛኝ ፍጡር ነህ! ፈሪ! በማስፈራራት ሰውን የግልህ ለማድረግ የምትጥር፡፡

/ካሌብ ለዱላ በመጋበዝ ማርታን በጥፊ ይመታታል፡፡ ማርታን በጥፊ ሲመታት ያዩ ሴቶችና ወንዶች(አምስት ወንድና አራት ሴቶች ያህል ) እየተንደረደሩ ለመገላገል ይመጣሉ፡፡ ቢኒያምም በሁኔታው ደንግጦ ካሌብ እያጣደፈ ከአካባቢው ያርቀዋል፡፡/

ቢኒያም፡- ምን ነካህ ካሌብ በጤናህ ነው?

ካሌብ፡- ጤና? ጤና ከራቀኝ ቆይቻለሁ፡፡ አሁን የመታሁት ቀንደኛ በሽታዬን እኮ ነው!

ቢኒያም፡- በጣም ተሳስተሃል እንዲህ ማድረግ አልነበረብህም፡፡

ካሌብ፡- ስህተት የምን ስህተት፣ ትክክል ነው ያረኩት፣ የታባቷ ብርቅ ነው እንዴ መፈቀር፡፡

ቢኒያም፡- እንዲህ አይደረግም፡፡

በማግስቱ ካሌብ በከባድ ራስ ምትሃት ተይዞ ነቅቶ ዶርም ውስጥ ቁጭ ብሎ ትዕይንቱን ይጀምራል፡፡

አቢ፡- ብለህ ብለህ አፈቀርኩ በሚል ሰበብ ከዶርም ሰው አስጠርቶ መማታት ጀመርክ?

ካሌብ፡- ስለማን ነው የምታወራው?

አቢ፡- ስላንተ ነዋ ሌላ ሰው አለ?

ካሌብ፡- ማን ነው የመታሁት የት ቦታ?

አቢ፡- ራሴን ስቼ ወይም በመንፈስ ተነድቼ እንደማትል አምናለሁ፡

ካሌብ፡- ምን ያውረገርግሃል ለምን በግልፅ አታወራም፡፡

አቢ፡- ትናንት እስከሚበቃህ መጠጥ ተግተህ መጥተህ ማርታን ከዶርም አስጠርተህ አልመታሃትም፡፡

ካሌብ፡- ማ! እኔ! እኔ ካሌብ ወንዱ!

አቢ፡- አይ እኔ አቢ ሴቷ ነኝ!

ካሌብ፡- አትቀልድ እንደዚያ አድርጌአለሁ እንዴ?

አቢ፡- በደመነፍስ ነበር እንዴ የምትንቀሳቀሰው?

ካሌብ፡- ሞት ይሻለኛል ማርታን ማርታን መታኋት? በነዚህ እጆች

አቢ፡- አዎ ግጥም አድርገህ ቢኒያም እንደነገረኝ ሰው ባይደርስ ኖሮ በጣም ትጎዳት እንደነበር ነው፡፡

ካሌብ፡- ኦ! ትልቅ ሀጢያት እስከዛሬ እንዲህ ተሳስቼ አላውቅም ምን ነካኝ?

አቢ፡- ለኔም በጣም ገርሞኛል ፈፀሞ ተለውጠህብኛል፡፡

ካሌብ፡- እኔ… ሰውን መምታት … ለዚያውም የማፈቅረውን …/ ቢኒያም ከውጭ ዳቦ ይዞ ይገባል፡፡ ከካፌ መሆኑ ነው/

ቢኒያም፡- ካሌብ እንዴት ነህ ካፌ አትሄድም እንዴ

ካሌብ፡- ምን ለማድረግ?

ቢኒየም፡- ቁርስ ለመብላት ነዋ?

ካሌብ፡- እ…እ… ይለፈኝ፡፡ ግን ቢኒ ማታ ማርታን መታኋት እንዴ? የማላምነው ጉድ፡፡

ቢኒያም፡- ከርቀት ስከታተላችሁ ነበር እንደ ድንገት በጥፊ መተኃት፡፡

ካሌብ፡- ማን እኔ?

ቢኒያም፡- ምን ሰይጣን እንደቀረበህ አላውቅም፡፡ እኔማ ሀናን ካፌ አግኝቻት ሁኔታውን እንድታረጋጋ ተማፅኛታለሁ፡፡

ካሌብ፡- ማለት የምን ማረጋጋት?

ቢኒያም፡- ማርታ ልትከስህ አስባለች አውላላ ሜዳ ላይ መተሃት እንደማትለቅህም ዝታለች፡፡

ካሌብ፡- ትክሰሰኝ መባረር ነው ሌላ ምን አለ? እሷን የመሠለም አጥቻለሁ እንኳን ትምህርት፡፡

አቢ፡- ምን ማለትህ ነው፤ ሴቶች አሻንጉልቶችህ አልነበሩም እንዴ ማርታ አልሸነፍ አለችህ፤ የተገላቢጦሽ አሻንጉሊቷ ሆንክ?

ቢኒያም፡- አንተ ዝም በል ቀልድ አያስፈልግም፡፡

ካሌብ፡- ልክ ነህ ተሸንፌያለሁ ሁሉም ነገር አስጠልቶኛል እሷን ካላገኘሁ እሞታለሁ፡፡

ቢኒያም፡- በቃ አስጠርተህ ይቅርታ ጠይቃት፡፡

ካሌብ፡- በምን አይኔ አያታለሁ እልኬን አስጨርሳኛለች አፍቅሬያታለሁ እስከ ሞት ድረስ ወድጃታለሁ፡፡

ቢኒያም፡- ምን? እውነትህን ነው?

ካሌብ፡- አዎን እስከዛሬ እንደ እሷ ሰው ወድጄ አላውቅም፡፡

ቢኒያም፡- ግን እኮ በመልክ እስከ ዛሬ ከምታውቃቸው ሴቶች አንዷንም አታህልም፡፡

ካሌብ፡- መልኳ አይደለም ባክህ የረታኝ፡፡ ማንነቷ፣ አልበገር ባይነቷ የአቋም ፅናቷ ነው ያሸነፈኝ፡፡

አቢ፡- ታዲያ ምን ተሻለ? ማፍቀር እድል መፈቀር እዳ ነው አሉ? እማማ አስካሉ፡፡

ቢኒያም፡- አንተ ደግሞ ትቀባጥራለህ፤ በማያስፈልግ ቦታ ትፈላሰፋለህ፡፡

አቢ፡- እውነት!! እኔም ፍቅር እንዲይዘኝ አማረኝ፡፡ ፍቅር ደስ የሚል ስቃይ ይመስለኛል፡፡ የሚጣፍጥ ስቃይ፡፡ ሳስበው ሳስበው ግን ፍቅር የሚባል ነገር በሲሪንጅ ቢሰጠኝም የሚይዘኝ አይመስለኝም፡፡

ቢኒያም፡- እንደ ማርታ ነህ ማለት ነው፡፡

ካሌብ፡- ማርታን አትጥራት፡፡

ቢኒያም፡- እሽ አላለችህም ጠበቃ ልትሆንላት ነው?

ካሌብ፡- ቢሆንም እወዳታለሁ አፈቅራታለሁ ማንም እንዲነካት አልፈልግም

ቢኒያም፡- እንዲህ ከሆንክላት በኋላ ግን እሺ ልትልህ ይገባ ነበር፡፡

ካሌብ፡- ግዴታ የለባትም፡፡ ግን አንድ ነገር አድርግልኝ ይቅርታ ጠይቅልኝ በኔ ስም

ቢኒያም፡- ራስህ ለምን አጠይቃትም?

ካሌብ፡- አይኗን ማየት አይቻለኝም፡፡ ማርታ ጉድ ሰርታኛለች፡፡ ተጫውታብኛለች፡፡

አቢ፡- ተረጋጋ ባለም ላይ የሌለ ነገር አንተ ላይ አልሆነም፡፡

ካሌብ፡- ችግሩ እኔ የምቀበለው አለመሆኑ ነው፡፡ ጨርሶ የማይዋጥልኝ፡፡

ቢኒያም፡- አቢ ና እስኪ አንድ ነገር ላማክርህ /ቢኒያምና አቢ ተያይዘው ይወጣሉ ካሌብ ብቻውን ይቀራል/

----------//------------

በሌላ ቀን ካሌብ በወሰደው የመድሃኒት ብዛት ተዳክሞ ሆስፒታል ገብቷል፡፡ ቢኒያምና አቢ እጅግ ተጨንቀዋል፡፡ ካሌብ መድሃኒት ከመውሰዱ በፊት ለማርታ እንዲሠጥለት የፈለገው መልዕክት አቢና ቢኒያም ይዘው

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

# BDU colorfully celebrated the 10th Ethiopian Nations, Nationalities and Peoples Day (Photo Gallery)











ለዝርርዝሩ ገጽ 4ን ይመልከቱ

# ጉድ ሰራችኝ ...

ከገጽ 15 የዞረ

ወደ ማርታ እያመሩ የመጨረሻው ትዕይንት ይጀምራል፡፡

ቢኒያም፡- ማርታ! ማርታ!

ማርታ፡- አቤት! (በተደናገረ ስሜት እያየችው)

ቢኒያም፡- መልዕክት አለሽ

ማርታ፡- የምን መልዕክት ?

ቢኒያም ፡- አንቺ አንብቢው መልዕክቱን ከውስጥ ታገኝዋለሽ

/የሰጣት ወረቀት ሰትገልጠው እንዲህ ይነበባል/

ማርታ፡- (ወረቀቱን ከፍታ ስታነበው በካሌብ ድምፅ እንዲህ ይነበባል፡ ፡) "ይህ የይቅርታ ደብዳቤዬ ነው፡፡ ለፈፀምኩት ስህተት ትልቅ ይቅርታ እንድታደርጊል እማፀንሻለሁ፡፡ አየሽ ማርታ ሳድግ ቤተሰቦቼ ሁሉን ማድረግና እንደምችል ምንም ነገር እንደማያሸንፈኝ አድርገው ነው ያሳደጉኝ፡፡ እስከዛሬም ፈልጌ ያጣሁት ሽቼ ያላገኘሁት ነገር የለም ነበር፡፡ በተለይ በፍቅር ግንኙነት ለሴት የነበረኝ ዝቅተኛ ግምት ሴትን እንደ ሰው ሳይሆን እንደ አሻንጉሊት እንድቆጥር ያደረገኝ ነበር፡ ፡ አንቺ ግን እንደዚያ ሆነሽ አላገኘሁሽም፡፡ ሴት ስትፈልግ እንጅ ሳትፈልግ እንቢ ማለት እንደምትችል ደጋግመሽ ነገርሽኝ፡፡ ከሁሉም በላይ በልበ ሙሉነት ምክንያታዊ ሆነሽ በወንድነት ትምህክት ላስፈራራሽ በሞከርኩ ጊዜ እንኳን ባለመረታት ተቋቋምሽኝ፡ ፡ እናም ፍፁም ልዩ ፍጡር ሆነሽ አገኘሁሽ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በጸታዋ ብቻ ከምንቃት እንስት በፍቅር ወደቅሁ፡ ፡ ወደድኩሽ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅርሽ አስረኛ ሆንኩ፡ ፡ እስከዛሬ የተማርኩት ትምህርት እንዲህ እንዳስብ አንዴም አላደረገኝም፡፡ ካንቺ ጋር የተገናኘሁበት አጋጣሚ ብዙ ነገር አስተምሮኛል፡፡ አሁን አንቺ ያልሺኝን አምኛለሁ፡ ፡ በፍቅርም ሆነ በማንኛውም ግንኙነት ሴትም ሆነ ወንድ አቻ ከተዋደዱ እና ከተቀራረቡ እንጂ በአስገዳጅነት የሚደረግ ፍቅር መኖር የለበትም፡ ፡ ግድ አፈቅሪኝ አልልሽም፡ ፡ ስለሰራሁት ስህተት ግን ይቅርታሽን አትንፈጊኝ፡፡ የምንግዜም አፍቃሪሽ ካሌብ ከሞት መንደር፡፡"

(ማርታ ተክዛለች፡፡ ወደ ቢኒያም እየተመለከተች ንግግሯን ጀመረች፡፡)

ማርታ፡- ቢኒያም ካሌብ የት ነው?

ቢኒያም፡- ሆስፒታል

ማርታ፡- ምን ... ምን ሆኖ?

ቢኒያም፡- ራሱን ለማጥፋት በወሰደው የመድሃኒት ብዛት ራሱን ስቶ ሆስፒታል ተኝቷል፡፡ ማረታ የሌለችበትን ህይወት መኖር አልፈልግም እያለም ነበር፡፡

ማርታ- ሌላ ስህተት ሰራ፡፡ እባክህ አብረን ሆስፒታል እንሂድ፡፡

ቢኒያም፡- ይቅርታ አደረግሽለት?

ማርታ፡- እንዴት አላደርግለትም? በተለይ ያ አጉል ትምክህቱን ከተወና ሴትም ልክ እንደ ወንድ በአለም ላይ እሷን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በራሷ መወሰን እንደምትችል ካመነ ከተገበረ ለምን ይቅር አልለውም፡፡

ቢኒያም፡- እልሁ ነው እዚሁ ያደረሰው፡ ፡ በሳት ለመጫወት የጀመረው ቀልድ፡፡

ማርታ፡- እንዴት?

ቢኒያም፡- ማንም እኔን እንቢ ማለት አይችልም እያለ የያዘው አቋም ነው ለዚህ ያደረሰው፡፡

ማረታ፡- አሁን ያለነው ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ቢያንስ የተማረ ሰው የተሻለ መሆን ይገባዋል፡፡ ለመሆኑ የሚተርፍ ይመስልሃል?

ቢኒያም፡- ይመስለኛል!! ለማንኛውም አብረን ሄደን እንየው፡፡

(ሶስቱም ተከታትለው ወጡ)

ኅህ ማተሚያ ቤት ታተመ